በኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ
ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት
የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፓነል ።

የወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁ.1569/74

ሐምሌ 30 ቀን 1977 ዓ.ም.

ዳኞች ፡ አቶ አሰፋ ሊበን
አቶ አበበ ወርቄ
ቀኛዝማች እንዳለው መንገሻ
አቶ ዓለማየሁ ኃይሌ
አቶ ደሳለኝ ዓለሙ

ይግባኝ ባይ . . . . ድሪባ አቦልቴ ከወህኒ ቤት በአጃቢ ቀረበ

መልስ ሰጭ . . . . አቃቤ ሕግ መሐመድ ሲራጅ የጠቅላይ ፍ/ቤትና የፓነል ችሎት አቃቤ ሕግ ኃላፊ ቀረበ

ጉዳዩ፡ . . . ተደራራቢ ጥፋቶችንና ተደራራቢ ቅጣትን በሚመለከት የቀረበ ክርክር

## ው ሳ ኔ

ድሪባ አቦልቴ በሁለት የተለያዩ ወንጀሎች ተከስሶ የከፍተኛው ፍ/ቤት ሁለቱን ክሶች በተለያዩ መዝገቦች አይቶ

1. እሸቴ ወልደየስን ለመግደል ግብረ አበር በመሆንና በዘረፋ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/522/1/ሀ በወንጀል መዝገብ ቁጥር 27/72 በአሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ፈርዶበታል ።

2. ወታደር ይገዙ ተክሌን በመግደልና በመዝረፍ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/1/ሀ/522/1/ሀ ፤ 668 በተከሰሰበት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 341/72 በሞት እንዲቀጣ ፈርዶበታል ።

ድሪባ አቦልቴ በሁለቱም መዝገቦች ውሳኔዎች ለየብቻ ይግባኝ አቅርቦ ፡

1. እሸቴ ወልደየስን ለመግደል ግብረአበር በመሆንና በዘረፋው ወንጀል ክስ ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ወንጀል መዝገብ ቁጥር 1067/73 ተሻሽሎለት እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ በአሥር ዓመት ጽኑ እሥራት ሲፈረድበት ፡

2. ወታደር ይገዙ ተክሌን በመግደልና በመዝረፍ ወንጀል ክስ ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1569/74 የሞቱ ቅጣት ተሻሽሎለት በአሥር ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ፈርዶበታል ።

ድሪባ አቦልቴ አሁን በአቤቱታ የቀረበው ፍርድ የተሰጠኝ እጄ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ ተብሎ በመሆኑ ፡ እጄ የተያዘበት ቀን በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1569/74 ባለመገለጹ ወህኒ ቤቱ ችግር ስለፈጠረብኝ ፡ እጄ የተያዘበት ቀን በ15/11/71 መሆኑ በሌላው ቁጥር 1067/73 የይግባኝ መዝገብ ውስጥ ማስረጃ ስለሚገኝ ከዚያኛው መዝገብ ውስጥ ታይቶ ለወህኒ ቤት በደብዳቤ ይገለጽልኝ ብሎ በ21/10/76 ባቀረበው ማመልከቻ መሠረት ነው ። አቃቤ ሕግ በድሪባ በኩል ለቀረበው ማመልከቻ መልሱን እንዲሰጥ ታዝዞ በሰጠው መልስ ላይ ፡

— ድሪባ የተያዘው በ5/11/71 መሆኑን የገለጸ ሲሆን ፣ የከፍተኛው ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 27/72 እጁ የተያዘው በ5/1/71 መሆኑን ገልጿል ። ሁለቱም የጠቅላይ ፍ/ቤት መዝገቦች ይህን አልጠቀሱትም ፤ ስለዚህ ጉዳዩን ያጣራው ፖሊስ ማስረጃ እንዲያቀርብ ይታዘዝ ፤

— በከፍተኛው ፍ/ቤት ሞት የተፈረደበት በሌላ መዝገብ አሥራ አምስት ዓመት የተፈረደበት መሆኑን በሪኮርድነት እቃቤ ሕግ አቅርቦ ካስረዳ በኋላ ነው ፤ ስለዚህም በይግባኝ ባይ ላይ ሞት የፈረደበት ሪኮርዱ ስለቀረበለት መስሎ ይታያል ።

— ጠቅላይ ፍ/ቤት ድሪባ አሥራ አምስት ዓመት በተፈረደበት ጉዳይ የቀረበለትን ይግባኝ ለብቻው በመመርመር ነው ወደ አሥር ዓመት ዝቅ ያደረገለት ፤

— እንዲሁም ጠቅላይ ፍ/ቤት ድሪባ የሞት ፍርድ በተፈረደበት ጉዳይ የቀረበለትን ይግባኝ ለብቻው በመመርመር ነው ወደ አሥር ዓመት ዝቅ ያደረገለት ።

— በጠቅላይ ፍ/ቤትም ደረጃ ሁለቱ መዝገቦች ተጣምረው ባለመቅረባቸው ነው የተለያየ ቅጣት የተሰጠው ፣ በማለት ሁኔታውን በመዘርዘር አስቀድሞ ይህ ፍ/ቤት ሁለቱን ቅጣቶች አዳምሮ የድሪባ አቦልቱ ቅጣት ሃያ ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲሆን አመልክቷል ። ለዚህም ያቀረበው የሕግ ትንታኔ እንደሚከተለው ነው ፦

— ጉዳዩን በቀጥታ የሚሸፍን አንቀጽ ባይኖርም ተቀራራቢ የሆነው አንቀጽ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 191 ነው ። ይህን አንቀጽ አንድ ወንጀል ከብዙ ወንጀሎች ጋር ተፈጽሞ ሲገኝና ወንጀለኛው የተቀጣው በአንዱ ወንጀል ብቻ ሲሆን ፣ ከተቀጣ በኋላ ግን ሌሎቹን ወንጀሎች መፈጸሙ ሲገለጽ ተፈጻሚነት ያለው እንደሚሆን በመግለጽ ፣ እንዲሁም

— ለዚህ ዓይነት ሁኔታ ቀጥር 189/1/ ተፈጻሚ ይሆናል በማለት ተደራራቢ ወንጀሎች በሚፈጸሙበት ጊዜ ቅጣት የሚወሰነው በምን ዓይነት እንደሆነ አንቀጹን በመተንተን ፣ እንዲሁም መሠረት ተደርጐ መያዝ ያለበት በሕጉ የተመለከተው ጣሪያ ቅጣት እንጂ ጥፋተኛው በአንቀጹ የተወሰነበትን ቅጣት እንደማይመለከት በመግለጽ ፣

— የጠቅላይ ፍ/ቤት ፓነል ችሎት ሌላው የጠቅላይ ፍ/ቤት ችሎት የሰጠው ውሳኔ ቀርቦለት ቢሆን ኖሮ ከባድ ቅጣት የሚያስከትለው በሌላው ችሎት የቀረበው ክስ ስለነበረና ቅጣቱም የሞት ቅጣት ስለነበረ ፓነል ችሎት የወንጀለኛ መቅጫን ሕግ ቁጥር 191ን እና 189ን በመከተል ሁለቱ ተደምረው ከሞት ቅጣት በታች ስለሆኑ ራሱ በያዘው መዝገብ የወሰነውን አሥር ዓመት ሌላው ችሎት ከወሰነው አሥር ዓመት ጋር ደምሮ 20 ዓመት ይወስን ነበር ።

— በሕግ የተመለከተ ሌላ አማራጭ ስለሌለ አሁንም ፓነል ችሎት የሌላው ችሎት ውሳኔ ቀርቦለት ቢሆን ኖሮ አዳምሮ ሃያ ዓመት መወሰን እንደሚችል ካስረዳሁ ከፍርድ በኋላ ጉዳዩ ከታወቀ ሁለቱ ቅጣቶች እንዲዳመሩ የማይደረግበት ምክንያት የለም ። በልዩ ልዩ ጥፋቶች የተወሰኑትን ቅጣቶች ማዳመር የስሌት ጉዳይ እንጂ አዲስ ቅጣት እንደመወሰን የሚቆጠር አይደለም ።

— ከዚህም በቀር ጸረ—አብዮተኞች የካቺሴን ከተማ ሲዘርፉና ሲወርሩ ይግባኝ ባይም በነፍስ ግድያውና በዘረፋው ወንጀል ግብረአበር መሆኑ ሲታወቅ

በሕግ ብቻ ሳይሆን በሕሊና ዳኝነትም ሲታይ የሃያ ዓመት ጽኑ እሥራት ቅጣት ሲያንሰው እንጂ አይበዛበትም በማለት ፣

— ይግባኝ ባዩ እጁ የተያዘበት ቀን ከተረጋገጠ በኋላ የሚፈጽመው ቅጣት ሃያ ዓመት ጽኑ እሥራት መሆኑ ተገልጾ ለወህኒ ቤት እንዲተላለፍ ሲል ጠይቋል ።

ድሪባ አቦልቴ የመጀመሪያው ጥያቄው ቀን ብቻ ተገልጾ እንዲጻፍለት ጥያቄውን እንደተራ ጥያቄ አድርጐ ያቀረበው ስለነበር አቃቤ ሕጉ ለሰጣቸው የሕግ ሃሳቦች መቃወሚያ አቅርቧል ። መቃወሚያውም በከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩ ሳይጣመር የታዬ መሆኑን ፣ ፓነል ችሎት ግን ሁለቱን መዝገቦች ዓይቶ የወሰነ መሆኑን ከፍተኛው ፍ/ቤት መጀመሪያ አሥራ አምስት ዓመት ፈርዶበት በሁለተኛው መዝገብ ላይ ደግሞ የሞት ቅጣት መበየኑ ውሳኔዎቹ ለየብቻ ሊፈጸሙ ስለማይችሉ ቅጣቱን አጣምሮ ውሳኔ መስጠቱን ስለሚያሳይ ፓነል ችሎት በውሳኔው መሠረት በጠቅላላው እንድታሠር የፈረደብኝ አሥር ዓመት ነው በማለት ተከራክሯል ።

በድሪባ አቦልቴ ላይ በሁለቱ መዝገቦች የተሰጡት ውሳኔዎች ድሪባ እንደሚለው ቅጣቱ ተጣምሮ ነው የተወሰነው ወይስ በሁለቱ መዝገቦች ላይ ውሳኔዎቹ የተሰጡት ለየተናጠል ነው ፣ የሚለውን ጥያቄ አስነስቷል ።

የከፍተኛው ፍ/ቤት አቃቤ ሕግ የመጀመሪያው የወንጀል ውሳኔ በሪኮርድነት የቅጣት ማክበጃ እንዲሆን ጥያቄ አቅርቦ እንደነበር ከመጀመሪያው የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ ላይ እንረዳለን ። ሁለቱም ወንጀሎች በአንድ ቀን በሁለት ሰዓት ልዩነት የተፈጸሙ በመሆናቸውና ለእነዚህ የወንጀል ድርጊቶችም ሁለቱም ክሶች የተመሠረቱት ድሪባ በሐምሌ 11/71 ከታሰረ በኋላ በመሆኑ ፣ አንደኛው የወንጀል ውሳኔ ለሌላው በሪኮርድነት ተጠቃሽ ሊሆን የማይችል ቢሆንም ፣ ፍርድ ቤቱ በሁለተኛው ወንጀል ላይ ቅጣቱን ሲወስን የመጀመሪያውን ቅጣት በሪኮርድነት ይያዘው ወይም በተደራራቢ ወንጀልነቱ ቅጣቱን ተምኖ ይያዘው ሳይገለጽ በሁለተኛው ክስ ላይ የሞት ፍርድ ፈጽኗል ። በመጀመሪያው ክስ ላይ ይግባኙ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ቀርቦ ችሎቱ የአሥር ዓመት ጽኑ እሥራት ሲወስን በሁለተኛው ክስ ላይ የነበረው ይግባኝ ደግሞ በጠቅላይ ፍ/ቤት ሌላ ችሎት የተሰጠ ውሳኔ ለመኖሩ በወግ የተገለጠ ጉዳይ ባለመኖሩ በፓነሉ ችሎት ቀርቦ የፓነሉ ችሎትም በሁለተኛው ይግባኝ ላይ የአሥር ዓመት እሥራት የተናጠል ፍርድ ሰጥቷል ። የውሳኔ አሰጣጡ ሁኔታ ይህ ሲሆን ድሪባ አቦልቴ የፓነል ችሎት በሁለተኛው ክስ አሥር ዓመት የቀጣኝ የመጀመሪያውን የሌላ ችሎት አሥር ዓመት ውሳኔ ከተመለከተ በኋላ ነው የሚለውን ክርክር የምንቀበለው አልሆነም ።

በሁለቱም ፍ/ቤቶች ውሳኔው በተናጠል የተሰጠ ነው ከሚለው በመነሳት ለሁለቱም የወንጀል ድርጊቶች መነሻ ቀኑ አንድ ቀን ሲሆን ፣ ይህ ሁኔታ ብቻ ለወህኒ ቤቱ ቢገለጽ ምን እንደሚያስፈጽም ጥያቄ ማቅረቡ አስፈላጊ መስሎ ስላታየን ላደረግነው ጥያቄ የወህኒ ቤቱ የአስተዳደር ክፍል ኃላፊ የሆኑት ፲ አለቃ አበራ መንግሥቱ በሁለቱ መዝገብት ላይ የተወሰኑትን ሁለት አሥር ዓመቶች በማዳመር በሃያ ዓመት እሥራት እንዲቀጣ እናደርጋለን ፣ ደጋጋሚ ወንጀለኛም እንደሆነ ተቆጥሮ አመክሮ አይሰጠውም በማለት መልሰዋል ።

ከዚህ በላይ እንደታየው የድሪባ ጥያቄ ድሪባ በሁለተኛው ወንጀል እሥራቱን መቼ እንደጀመረ ቀኑን የመግለጽ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ድሪባ በሁለቱ መዝገቦች በአጠቃላይ ምን ያህል ጊዜ መታሠር እንዳለበት መልስ የመስጠት ጉዳይ ሆኖ

አግኝተነዋል ። በሁለቱም መዝገቦች ላይ የወንጀሉ ድርጊት የተፈጸመው አንድ ቀን በመሆኑ ድሪባ በመጀመሪያው ወንጀል ከታሠረ በኋላ ከእሥራት ሳይለቀቅ ሁለተኛው ክስ ተመስርቶበት የተፈረደበት በመሆኑ ሁለቱንም የአሥር ዓመት ፍርዶች ጎን ለጎን ነው የሚፈጽመው ፤ ማለትም በሁለቱም መዛግብት ሊታሠር የሚገባው ሁለት አሥር ዓመት ሳይሆን አንድ አሥር ዓመት ብቻ ነው ? ወይንስ ሁለቱ ቅጣቶች ተዳምረው ማለትም በሃያ ዓመት እሥራት ይቀጣል ? ወይንስ ሌላ ሶስተኛ አማራጭ አለ ? ሕጋችን ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሆን የለውም ቢባል ፍርድ ቤቱ ከነዚህ አማራጮች አንደኛው ይሁን ቢል ቀድሞ ያልተበየነውን አዲስ ውሳኔ መስጠት አይሆንም ወይ ? የሚሉትን ጥያቄዎች ያስነሳል ።

አንድ ሰው በወንጀል ተከስሶ የተፈረደበት እሥረኛ መሆኑ ሳይገለጽ አንድ ፍ/ቤት በዚሁ ሰው ላይ የሌላ የወንጀል ክስ ሰምቶ ውሳኔ ቢሰጥ ቅጣቱ እንዴት ነው የሚፈጸመው ለሚለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕጋችን መልስ የሚሰጥ ሆኖ አናገኘውም ። ስለዚህ ጉዳይ የሚያወሳ ሕግ የለም በማለት ብቻ ደግሞ ፍርድ ቤቱ ለቀረበለት ጥያቄ መልስ ሳይሰጥ ለማለፍ አይችልም ። በሌላ በኩል የቅጣት አፈ ጻጸም የወህኒ ቤት ጉዳይ በመሆኑ ቀኑን ገልጸን እንቀመጥ እንዳይባል ወህኒ ቤት ማስፈጸም ያለበት ፍርድ ቤት የወሰነውን በመሆኑና በዚህ ጉዳይ ላይም ወህኒ ቤቱ ምን ያደርግ እንደነበር ለቀረበለት ጥያቄ የሰጠው መልስ ወይም መፍትሄ ሕጋዊ መሠረት ያለው መስሎ ስላልታየን ፣ ይህ ፍ/ቤት ጥያቄውን አስተናግዶ ስለቅጣቱ አፈጻጸም መስሎ የታየውን መመሪያ መስጠቱ አስፈልጓል ።

ለድሪባ አቦልቴ ሁለት የወንጀል ቅጣቶች መሠረት የሆኑት በአንድ ቀን በሁለት ሰዓት ልዩነት የፈጸማቸው የወንጀል ድርጊቶች ናቸው ። እነዚህ ድርጊቶች ሁለት የተለያዩ ክሶች ሊያስመሠርቱበት ይችላሉ የሚባል ቢሆንና ይህን ሁኔታም አቃቤ ሕግ በአንድ ጊዜ ቢደርስበት ኖሮ ተደራራቢ ክሶችን መስርቶበት የቅጣት አወሳሰኑም በወ.መ.ሕ. ቁጥር 189 መሠረት ይሆን ነበር ። ድርጊቱ በአቃቤ ሕግ ሳይታወቅ ቀርቶ ለሁለቱም ድርጊቶች በተለያየ ወቅት የተለያዩ ክሶች ቢመሠረቱበትና በአንደኛው ክስ ቀድሞ ውሳኔ ቢሰጥ እና ፣ ይህ ሁኔታ ግን ሁለተኛውን ክስ ለሚሰማው ፍ/ቤት ቢገለጽ ፍርድ ቤቱ ሁለተኛውን ቅጣት መወሰን ያለበት በወ.መ.ሕ. ቁጥር 191 መሠረት ይሆን ነበር ። በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ 191 መሠረት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን የሚከተለው መርህ በወ.መ. ሕግ ቁጥር 189 ላይ የተገለጸውን ለመሆኑ ይኸው አንቀጽ 191 ይገልጻል ። ለወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 189ም ሆነ ለወ.መ. ሕግ ቁጥር 191 የቅጣት አወሳሰን መሠረት የሚሆኑት ድርጊቶች ድሪባ አቦልቴ ፈጸማቸው የሚባሉት ዓይነት ድርጊቶች ናቸው ። እነዚህ አንቀጾች በድሪባ አቦልቴ ጉዳይ ላይ በቀጥታ ተጠቃሽ ሊሆኑ ያልቻሉት የድሪባ አቦልቴ የወንጀል ተግባር በተደራራቢ ክስነት ያልቀረበበት መሆኑ ወይም ተነጣጥሎ ከተከሰሰም በኋላ ይኸው ሁኔታ መኖሩ በወግ ተገልጾ ሁለተኛው ቅጣት ከአንደኛው ቅጣት ጋር ተገናዝቦ አለመሰጠቱ ብቻ ነው ። በመሆኑም ይህ ሁኔታ ሲፈጠር ፍርድ ቤቱ መመሪያ መስጠቱ አማራጭ የሌለው መንገድ ነው በተባለው መሠረት ለድሪባ አቦልቴ ጉዳይ በቅርብ ተጠቃሽ ሊሆኑ የሚችሉት አንቀጾች እነዚህ የወ.መ.ሕ. ቁጥር 189 እና 191 በመሆናቸው እነዚህኑ አንቀጾች በመተርጎም መመሪያ መስጠቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል ።

ቀደም ሲል እንደገለጽነው በአንቀጽ 191 መሠረት የሚደረግ የቅጣት አወሳሰን የሚከተለው በአንቀጽ 189 ላይ የተዘረዘረውን መርህ ነው ። ድሪባ አቦልቴ ፈጸማቸው ከተባላቸው ሁለት ወንጀሎች ውስጥ ከባዱ ጥፋት በወንጀል መዝገብ

ቁጥር 1067/73 የወ.መ.ሕ. ቁጥር 522ን በመተላለፍ ጥፋት ፈጽሟል የተባለበት ክስ ነው ። በወንጀል መዝገብ ቁጥር 1569/74 ጥፋተኛ የተባለው ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 8/67 አንቀጽ 3/2/ን በመተላለፍ በመሆኑ ለጥፋቱ በሕግ የተወ ሰነው ቅጣት ለመጀመሪያው ጥፋት በሕግ ከተወሰነው የሞት ቅጣት ያነሰ ነው ።

በወ.መ.ሕ. ቁጥር 522 መሠረት የቀረበውን ክስ በይግባኝ ሰምቶ የአሥር ዓመት እሥራት ውሳኔ የሰጠው የጠቅላይ ፍርድ ቤት ስድስተኛ ችሎት ነው ። ለከፍተኛው ጥፋት የተወሰነው ቅጣት ይህ የአሥር ዓመት ፍርድ ነው ብለን ብን ወስድ ለፓነል ችሎት ቀርቦ የታየው ጉዳይም ለዚሁ ስድስተኛ ችሎት ቀርቦ ቢሆን ኖሮ ቅጣቱ የሚወሰነው በዚህ በአንቀጽ 189/1/ለ / አነጋገር ይህን የአሥር ዓመት ፍርድ መነሻ በማድረግ ቅጣቱን ፍርድ ቤቱ ለቅጣቱ « . . . መሠረት አድ ርጐ ለያዘው ጥፋት በተወሰነው ከፍተኛ የቅጣት ዘመን ላይ የዚሁ የቅጣቱ ዘመን አጋማሽ እስኪሆነው ድረስ » በማሳደግ እንደሆነ ይኸው አንቀጽ ይገልጻል ። ይህም በስሌት ድሪባ አቦልቴ ሊቀጣ የሚገባው ቅጣት አሥራ አምስት ዓመት ሆኖ እናገኘዋለን ። የተደረቡ ወንጀሎች ሲያጋጥሙ ለከፍተኛው ቅጣት እወሳ ስን አንደኛው ገደብ ይኸው በጥቅስ ውስጥ ያስቀመጥነው የወ.መ.ሕ. ቁጥር 189/1/ / ለ / አካል በመሆኑ አቃቤ ሕግ ይህን በመጻረር ተደምሮ 20 ዓመት እሥ ራት እንዲቀጣ በማለት ያመለከተውን አልተቀበልነውም ።

የአዲስ አበባ ወህኒ ቤት በሁለት መዝገቦች ድሪባ አቦልቴ ላይ የተሰጡትን ፍርዶች ማስፈጸም ያለበት ከዚህ በላይ እንደገለጽነው አሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲታሠር በማድረግ መሆኑን ፣ ሁለቱም የወንጀል ቅጣቶች የተ ወሰኑት በአንድ ቀን በተሠሩ ተደራራቢ ወንጀሎች እንጂ ለአንድ ወንጀል ተወ ስኖበት ቅጣቱን በመፈጸም ላይ እንዳለ ወይም አንድ ጊዜ ቅጣቱን ጨርሶ ከወጣ በኋላ ሌላ ወንጀል እንደፈጸመ ደጋጋሚ ወንጀለኛ ተቆጥሮ አመክሮም እንሰጠ ውም ያለውን ባለመቀበል ፤ አመክሮው መታየት ያለበት እንደማንኛውም እሥ ረኛ በ ህኒ ቤት በሚያሳየው ጠባይና ሌሎች መመዘኛዎችን ማሟላት አለማሟ ላቱን በማየት ብቻ እንዲሆን በመወሰን ይህን የፍርድ ማብራሪያ ሰጥተናል ።

በዚህ ውሳኔ መሠረት እንዲፈጽም የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለአዲስ አበባ ወህኒ ቤት ይተላለፍ ።

ይህ ውሳኔ ዛሬ ሐምሌ 30 ቀን 1977 ዓ.ም. በፓነል ችሎት በድምጽ ብልጫ ተሰጠ ።

## የአነስተኛ ድምጽ አስተያየት

እኛ በሁለተኛና በአምስተኛ ተራ የተሰየምነው ዳኞች አበበ ወርቄና ደሳ ለኝ ዓለሙ ስለድሪባ አቦልቴ ቅጣት በድምጽ ብልጫ በተሰጠው የሕግ አተረጓ ጐምና የእሥራት ዘመን ውሳኔ አልተስማማንም ።

በእኛ አስተያየት ሊሰጥ የሚገባው ውሳኔ ነው ስለምንለው አስተያየታችንን እንደሚከተለው እናሠፍራለን ።

ድሪባ አቦልቴ በተከሰሰባቸው ሁለት የተለያዩ መዝገቦች በከፍተኛው ፍ/ቤት በአንደኛው በሞት እንዲቀጣ ሲፈረድበት ፣ በሌላው በአሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ተፈርዶበታል ። ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ ድሪባ

በሞት እንዲቀጣ የተፈረደበትን አሻሽሎ በአሥር ዓመት ጽኑ እሥራት ሲፈርድበት ፣ በአሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት የተፈረደበትን አሻሽሎ እንደዚሁ በአሥር ዓመት ጽኑ እሥራት ነው እንዲቀጣ የፈረደበት ። በሁለቱም ድርጊቶች ቅጣት የተወሰነበት እሥራቱን የሚፈጽመው እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ እየተቆጠረ እንዲሆን ነው ።

በሁለቱም መዝገቦች በሁለቱም ፍርድ ቤቶች በድሪባ አቦልቴ ላይ ቅጣት ሲወሰን በሌላው መዝገብ ላይ ያለው ጉዳይ ስለቅጣት ማክበድም ሆነ ስለቅጣት ማጣመር እንዳችም የተገለጸ ነገር የለም ። በዚህም መሠረት የአሁኑ ክርክር የተፈጠረው እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ አሥር ዓመት እንዲታሠር ሲወሰን እጁ የተያዘበት ቀን ስላልተገለጸ እጁ የተያዘበት ቀን በአንደኛው መዝገብ ውስጥ ቀኑ ይገኛል ፣ ይኸው ተጠቅሶ ለወህኒ ቤት ይተላለፍልኝ የሚለው የድሪባ አቦልቴ ጥያቄ በቀረበበት ፊቅት ነው ። ቀኑ ሐምሌ 11 ቀን 1971 መሆኑ ከመዝገቡ ሲገኝ ፣ ድሪባ አቦልቴ በሁለት ወንጀል የተከሰሰ በመሆኑ አቃቤ ሕግ አስተያየት እንዲሰጥበት በመደረጉ አቃቤ ሕግ ጥያቄው ቀን የመግለጽ ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ሁለቱ ቅጣቶች ተደምረው መታሰብ ስላለባቸው ሁለቱን ቅጣቶች አዳምራችሁ ቅጣቱ ይወሰን የሚል ጥያቄ አቀረበ ።

አቃቤ ሕግ ይህን ጥያቄ ሲያቀርብ በማመልከቻው ላይ በግልጽ ያስቀመጠውና የጠየቀው « . . . ጉዳዩን በቀጥታ የሚሸፍን አንቀጽ ባይኖርም ተቀራራቢ የሆነው አንቀጽ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ 191 . . . » ታይቶ በቁጥር 189 መሠረት እንዲወሰን ነው ።

አቃቤ ሕጉ በግልጽ እንደጻፈው በወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ላይ ይህን የሚሸፍን አንቀጽ የለም ። የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በተረቀቀበት ጊዜ ይህን ጥያቄ እንዲሸፍን ተደርጎ አልተረቀቀም ። ይህ ፍርድ ቤት በተመሳሳይ ጉዳዮች የተሰጡ ወሳኔዎች እንዳለም ፈልጎ አላገኘም ። የቀድሞ ፍርዶች አስገዳጅነት ባያኖራቸውም ለምርምር መርዳታቸውና ለውሳኔ ምክንያት ሊኖራቸው ስለሚችል መጥቀማቸው ስለማይቀር ቢኖሩ በረዱ ነበር ። ካንዳንድ ካየናቸው በኮድ ሕጎች በሚሠሩ «ለሎች አገሮችም ሕጎች ይህን የሚሸፍን አንቀጽ አላገኘንም። በፈረንሳይ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የዚህ ሃሳብ አተረጓጎም ሊመነጭ የሚችለው ከአንቀጽ 5 ሲሆን ፣ በፍርድ ጊዜ ካልተወሰነ በስተቀር ቅጣት ተከታታይ ሳይሆን ጎን ለጎን የሚሄድ መሆኑን ነው የሚያመለክት ። የቻይና ሪፓብሊክ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 50—53 ፣ የሶቪዬት ኅብረት የፌዴራል የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 35 እና 36 አስቀድሞ የተፈረደ ፍርድ ቅጣቱ ሳይፈጸም ሌላ ወንጀል ፈጽሞ ከተገኘ የኋለኛው ቅጣት በተደራቢ እንደሚፈጸም ፣ ድምር ቅጣቱ ግን ከተወሰነ ጣሪያ እንደማይበልጥ ይናገራሉ ። ሆኖም የቻይና ሪፓብሊክ የወንጀለኛ መቅጫ በአንቀጽ 53 በግልጽ እንደሚያስቀምጠው አንድ ተከሳሽ ከአንድ በላይ በሆኑ ወንጀሎች ቅጣት ከተፈረደበት ፣ ቅጣቶቹ በዚያው ሕግ አንቀጽ 51 መሠረት መጣመር እንዳለባቸውና አጠማመራቸውም ልክ አብረው እንደተፈረዱ ወይም የኋለኛው ፍርድ ሲፈረድ የመጀመሪያው ታውቆ ቢሆን ኖሮ እንደሚጣመሩ ሁሉ ቅጣቶች እንዲጣመሩ ተደርጎ መሆኑን ይገልጻል ።

በኢትዮጵያ ሕግ ተመሳሳይ አንቀጽ የለንም ። በሌላም በኩል ከአንዳንድ የምርምር ሥራዎች እንደሚታየው ኮሎምቢያ ሎው ሪቪው በተባለው የሕግ መጽሔት ቮሉዩም 25/1925 ገጽ 671—672 እንደተጠቀሰው አንድ ቅጣት ሌላው ቅጣት ሳያልቅ የሚቀጥል ስለመሆኑ በፍርድ ውስጥ በግልጽ ካልተመለከተ ቅጣ

ቶቹ ጎን ለጎን መፈጸም ያለባቸው መሆኑን ያጠቁማል ። ይህ አሠራር አስቸጋሪ የማይሆነው ሁለቱ ቅጣቶች የተወሰነባቸው ጥፋቶች በአንድነት በአንድ ፍርድ ቤት ታይተው በአንድ ጊዜ ሲወሰኑ ወይም በአንድ ጊዜም ባይቀርቡ የመጀመሪያው መወሰኑን የኋለኛውን የሚወስነው ፍርድ ቤት የሚያውቀው በሚሆንበት ጊዜ ነው ። የኢትዮጵያ ሕግም የሚከተለው ይህንኑ ዘዴ ነው ። በኢትዮጵያ ሕግ እንደሌሎቹ ሁሉ ችግር የሚፈጠረው የመጀመሪያውን የሚወስነውና የኋለኛውን የሚወስነው አንድ ፍርድ ቤት ሳይሆን ወይም አንዱ መወሰኑ ሳይታወቅ ሁለቱም ውሳኔዎች በተለያየ ጊዜ ተወስነው እፈጸሙ በሚኪሄድበት ጊዜ ታውቆ ጥያቄው ለፍርድ ቤት ሲቀርብ ነው ። ስለቅጣቶች መጣመርና አለመጣመር የተጻፉት የምርምር ወረቀቶች ጉዳዩ ከፍርድ ቤት ፍርድ ቤት ችሎት ችሎት የተለያየ ውጤት ላይ እንደሚያደርስም ይጠቁማሉ ። ሁለም የሚስማሙት ግን በግልጽ ተወስኖ ቅጣቱ ተከታታይ መሆኑ ካልተገለጸ ጎን ለጎን መሄድ ያለበት መሆኑን ነው ።

ክሪሚናል ሎው ሪቪው የተባለው የሕግ መጽሔት 1958 ገጽ 174 ላይ የተመለከተውም ይህንኑ ይደግፋል ። እንዲሁም ይኸው መጽሐፍ በ1962 እትሙ ገጽ 490—91 የተመለከተው ይህንኑ ይደግፋል ።

እንግዲህ ወደ ኢትዮጵያ ሕግ ስንመለስና የድሪባ እቦልቱን ጥያቄና የአቃቤ ሕጉን ተቃውሞና ጥያቄ ስናይ አቃቤ ሕግ ቮለሕጉ በገለጸው ላይ እንዳለው « . . . የአሁኑን ጉዳይ በቀጥታ የሚሸፍን አንቀጽ ባይኖርም . . . » ያለውን በቀጥታ እንስማማበታለን ። በሌላ በኩል ግን የቀረበውን ጉዳይ የሚሸፍን አንቀጽ ከሌለ ተቀራራቢነት ያለው አንቀጽ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 191 ስለሆነ ወንጀሎቹን የፈጸመው በአንድ ቀን በሁለት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ስለሆነ ክሶቹ ተጣምረው ባይቀርቡም ክሶቹ ተጣምረው ከሚቀርቡበት ጊዜ የበለጠ ቅጣት እንዳይደርስበት በማድረግ አንድ ቅጣት ይወሰናል ስለሚል እና ወደ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 189 ስለሚመራ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 189 መሠረት አይቶ ቅጣቱን 20 ዓመት ጽኑ እሥራት አድርጎ ይወስንልኝ የሚለው የአቃቤ ሕግ ጥያቄ በቀጥታ ስምምነት የሚሰጠው ሳይሆን ብዙ ሌሎች ጥያቄዎች የሚያስነሳ ነው ፤

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ 191 የሚናገረው አንድ ተከሳሽ በተከሰሰበት አንድ ወንጀል ተፈርዶበት ቅጣት ከተወሰነበት በኋላ ሌላ ጥፋት ፈጽሞ ተገኝቶ ቅጣት በሚወሰንበት ጊዜ ቅጣቱ ሲወሰን በአንድ ጊዜ ቢፈረድበት ኖሮ ከማወሰንበት ቅጣት የማይበልጥ እንዲሆን የሚያመለክት ነው ። በዚህም ጊዜ ስለአሠራሩ የሚመራው ወደ ወንጀለኛ መቅጫው ሕግ ቁጥር 189/1/ ሲሆን ቁጥር 189/7/ ደግሞ የቅጣት ማክበድን ደንቦች መከተል እንዳለብን ይደነግጋል ። ቁጥር 189/1/ በተጨማሪም የሚደነግገው ሁኔታው ባጋጠመ ጊዜ ቅጣቱ መክበድ ያለበት መሆኑን ፤ በሚከብድበት ጊዜም /1/ ከሁሉ ጥፋቶች ከባድ ለሆነው ጥፋት የተደነገገው ቅጣት መወሰን ያለበት መሆኑ /2/ አስፈላጊ ሆኖ ቢያገኘውም ቅጣቱን ከባድ ለሆነው ጥፋት የተወሰነው አጋማሽ እስከ ደረሰ ድረስ ሊያሳድገው የሚችል መሆኑ ተደንግጓል ።

አቃቤ ሕግ ከባድ ለሆነው ጥፋት የተወሰነው ቅጣት ሰል በሕጉ የተደነገገውን ጣሪያ እንጂ በፍርድ ቤቱ የተወሰነውን ቅጣት አይደለም በማለው በአሁኑ ክርክር የአንስተኛው ድምጽ አስተያየት ሊሰጥበት ሰላልፈለገ አልፈነዋል ።

ድሪባ አቦልቲ በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1569/74 የከፍተኛው ፍርድ ቤት ፍርድ ተለውጦ ሲወሰን « . . . እጁ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ እየታሰበ በ10 ዓመት ጽኑ እሥራት . . . » እንዲቀጣ ተብሎ ነው ። እንዲሁም በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1067/73 የከፍተኛው ፍ/ቤት ፍርድ ተለውጦ ሲወሰን « . . . አሻሽለን እጁ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በአሥር ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ » ተብሎ ነው ። ሁለቱ ፍርዶች በዚህ ሁኔታ እስካሉ ድረስ እንዲህ ቢሆን እንዲህ ይደረግ ነበር በማለት አንዱ ፍርድ አስቀድሞ ቢታወቅ ኖሮ ይከብድ ነበር ወደሚለው ለመሄድ አስቸጋሪ ሁኔታ ይታያል ። ሁለቱ ፍርዶች በጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጡ ናቸው ። ሁለቱ ፍርዶች በተለያየ መዝገብ ታይተው የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥባቸው ሁኔታው ከታወቀ መደረግ ያለበት ይኸ ነው ተብሎ የተደነገገ ነገር ሳይኖር ሁለቱን ቅጣቶች ሰርዞ ሌላ ቅጣት መወሰን የሚፈቀድበት ሁኔታ አልታየንም ። ቅጣቶቹንም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 189 መሠረት ለማዳመርና ለማክበድ እንደ ቁጥር 191 ያለ ፈቃጅ ሕግ ያስፈልጋል ። እንደ ቁጥር 191 ያለ ፈቃጅ ሕግ ከሌለ ዳኞች በራሳችን አስተያየት በቁጥር 189 የተመለከተውን እንከተል ብንል በቁጥር 191 ትይዩ የሆነ ሌላ ሕግ እንዳለ አድርገን ተጠቀምን ማለት ነው ። በመሆኑም ቅጣቱ የሚጀመርበት ቀን ተቆርጦለት የተወሰነውን ፍርድ በሌላ ፍርድ ተካን ማለት ነው ። የአቃቤ ሕግ ክርክር ሌላ ውሳኔ መኖሩ ቢታወቅ ኖሮ ፍርድ ቤቱ ሁለተኛውን ቅጣት ሲወስን ቅጣቶቹን ማዳመር ብቻ ስለሆነ አዲስ ቅጣት እንደወሰነ አያስቆጥረውም የሚል ነው ። ይህን ግን የምንስማማበት አስተያየት አይደለም ። አቃቤ ሕግ እንደሚለው ለመጀመሪያ ጥፋት የተወሰነው ቅጣት ቢታወቅም ኖሮ ፍርድ ቤቱ ለሁለተኛው ጥፋት ምን ይወስን እንደነበረ ያሁኑ ችሎት ማወቅ አይችልም ። ማወቅ ካልቻለም ችሎቱ የሚሰጠው የቅጣት ውሳኔ ከሁለቱ ውሳኔዎች የተለየ ውሳኔ ነው የሚሆነው ማለት ነው ። ይህም አዲስ ቅጣት እንደመወሰን ነው ማለት ነው ። በሌላም በኩል ችሎቱ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ችሎት እንደመሆኑ መጠንም ከፍተኛው ፍ/ቤት ቅጣቶቹን እንደገና እንዲወስን ይመልሰውም እንደነበረ ማወቅ አይቻልም ። ስለዚህም ጉዳዩን ያዩት ችሎቶች ያደርጉት የነበረው ግልጽ ስለሆነ በዚያው መሠረት ይወሰን የሚለውን የአቃቤ ሕጉን አመለካከት የአነስተኛ ድምጽ አስተያየት የሰጠነው ዳኞች ልናምንበት አልተቻለንም ። የአቃቤ ሕጉን አስተያየት ብንቀበለው አዲስ ፍርድ ፣ አዲስ ቅጣት መወሰን መስሎ ታይቶናል ። ይህም ደብል ጂኦፓርዲ ( double jeopardy ) ወይም ኦትርፏ አኩይ (autrefois acquit ) ወይም ኦትርፏ ኮንቪክት (autrefois convict) እየተባሉ ከሚጠሩ በኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫም ሕግ በቁጥር 2 ፣ 3 ፣ 60—63 የተመለከተውን በአንድ ድርጊት ሁለቴ ከመቅጣት ጽንሰ ሃሳብ ጋር የማይሰምር አሠራር መስሎ ስለታየን በድምጽ ብልጫ በተሰጠው አስተያየት አለመስማማቱን መርጠናል ።

በዚህም መሠረት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ወንጀሎች በአንድ ሰው ተፈጽመው ክሶቹ በአጋጣሚ ሁኔታ በተለያየ ጊዜ ታይተው በቅደም ተከተል ውሳኔ ከተሰጠባቸው ፣ ውሳኔ የተሰጠውም አቃቤ ሕግ ከሁለቱ ውሳኔዎች በአንዱ ቀደም ብሎ የቅጣት ውሳኔ መኖሩን ባለመግለጹ ወይም ፍርድ ቤቱ ሁኔታው ተገልጾለት ሆኖም በጥናቸውም ሁኔታ በስሕተት ካለፈውና በሁለተኛው ጥፋት ለብቻው የተለየ ቅጣት ከወሰነ ፣ ሁለቱም ውሳኔዎች ቅጣቱ የሚጀምርበትን ቀን እስከ ጠቀሱ ድረስ በውሳኔዎቹ መሠረት ከሚፈጸም በስተቀር ስለቅጣቱ ውሳኔ ተለዋጭ ውሳኔ ማስፈር የሚቻልበት መንገድ አልታየንም ።ድሪባ አቦልቱ በጠየቀው መሠረት እጁ የተያዘበት ቀን ብቻ ተገልጦ በውሳኔዎቹ መሠረት እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ እሥራቱ ጎን ለጎን እየሄደለት እንዲፈጽም ከማድረግ

በስተቀር የአቃቤ ሕጉን ጥያቄ ተቀብሎ ቅጣቱን ወደ ሃያ ዓመት መለወጥ አይ ቻልም የሚል ነው አስተያየታችን ።

ስለሁኔታው ለማጣራት ከአዲስ አበባ ወሀኒ ቤት የጠራናቸው መኮንን ሁለት ውሳኔ ካገኘን ፡ ሁለቱንም ቅጣቶች በማዳመር ነው የምናስፈጽመው ፡ እንዲያ ውም ደጋጋሚ ጥፋተኛ አድርገን ነው የምንቆጥረው ፤ በዚህም መሠረት አመክሮ እንኳን አንጠይቅለትም ፤ ብለው አስተያየት ሰጥተውናል ።

ድሪባ አቦልቴ በዚህ ላይ ሃሳብ ሲሰጥ ወሀኒ ቤት እሥራት ከሚያስፈጽም በስተቀር የሕግ አስተያየት ሊጠየቅ አይገባውም ነው ያለው ። በአነስተኛው ድምጽ አስተያየት የአዲስ አበባ ወሀኒ ቤት ተወካይ የሰጡትን ሃሳብ መቀበል ያዳግታል ። ግልጽ የሆነ ሕግ ባለበት ቦታ እንዲህ የተዘጋጀ መልስ ሊሰጥ የሚቻልም አይመስ ለንም ። የአመክሮ መብት የማስጠቱም ጉዳይ አሳሳቢ ሆኖ ነው የምናገኘው ። በዚህም ላይ ቢሆን ወሀኒ ቤቱ እሥረኛው ሌሎች ሁኔታዎችን ካሟላ አመክሮ ሊጠ የቅለት የሚገባ ነው የሚመስለን ።

በእነኝህ ሁሉ ምክንያቶች በድምጽ ብልጫ በተሰጠው የአሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት ውሳኔ ባለመስማማት ድሪባ አቦልቴ እጁ የተያዘው በሁለ ቱም ክሶች በሐምሌ 11 ቀን 1971 መሆኑ ተገልጾ ከላይ በሰጠነው አስተያየት መሠረት እንዲፈጸም ነው ለወሀኒ ቤት መተላለፍ የነበረበት በማለትና ስለሕጉ ሁኔታም በአሁኑ ወቅት ያለው የሕግ አሻሻይ ኮሚቴ ቢያውቀው የሚጠቅም ይመ ስለናል በማለት የአነስተኛ ድምጽ አስተያየታችንን አስፍረናል ።

## ነጻነትን በሚያሳጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ጉዳይ የቅጣት አወሳሰን ፤ በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1569/74 በተሰጠ ፍርድ ላይ የቀረበ ትችት ።

በንጋቱ ተስፋዬ *

በዚህ የሕግ መጽሔት ውስጥ ታትሞ በወጣው በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1569/74 ፣ ፍርድ ቤቱን የተደራራቢ ወንጀሎች ጉዳይ የገጠመው ሲሆን ፣ የተነሱት ጭብጦችም

1/ በተደራራቢ ወንጀሎች ጉዳይ ቅጣቱ እንዴት መወሰን ይኖርበታል ?

2/ አንድ ወንጀለኛ ተደራራቢ የወንጀል ድርጊቶች በመፈጸሙ ምክንያት በተለያዩ ፍ/ቤቶች ፣ ወይንም በተለያዩ የአንድ ፍ/ቤት ችሎቶች ፣ ለተለያዩ የተወሰኑ ዘመናት በእስር ቤት እንዲቆይ በተናጠል ሲፈረድበት ፣ ውሳኔዎቹ እንዴት መፈጸም ይኖርባቸዋል ?

3/ በተራ ቁጥር / 2 / በተገለጸው ሁኔታ ፣ አንድ ፍ/ቤት የቅጣቶቹ አፈጻጸም ከተጀመረ በኋላ ቅጣቱን ቢያከብድ ፣ አዲስ ቅጣት እንደመጣል ይቆጠራል ?

የሚሉ ነበሩ ።

በእኛ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ በቁጥር 82/1/ / ሀ / እንደተገለጸው ፣ « መደራረብ » ሁለት ዓይነት ነው ፤ ግዙፋዊና ጣምራዊ ።

አንድ ወንጀለኛ ብዙ የወንጀል ድርጊቶችን በማከታተል[1] ሲፈጽም ፣ ግዙፋዊ መደራረብ ይኖራል ። ተከታታዮቹ የወንጀል ድርጊቶች በባህርያቸው አንድ ዓይነት ወይንም የተለያዩ መሆናቸውም ሆነ ፣ በአንድ ሰው ወይንም በብዙ ሰዎች ላይ መፈጸማቸው ምንም ልዩነት አይፈጥርም ። ለምሳሌ ፣ « ወ » « ተ » ን በማስገደድ የሩካቤ ስጋ ቢፈጽም እና ፣ ቀጥሎም የአንገቷን የወርቅ ሀብል በኃይል ቢቀማት ፣ በአንድ ሰው ( ማለትም በ « ተ » ) ላይ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 589ን እና 636ን በመተላለፍ የተለያዩ ባህርያት ያላቸው ተደራራቢ የወንጀል ድርጊቶች ይፈጸማል ። በተመሳሳይ ሁኔታ ፣ « ወ » በ « ሀ » ላይ የእጅ እልፊት ቢፈጽምበትና ፣ ከ « በ » ሚስት ጋር ደግሞ የሩካቤ ስጋ ግንኙነት ቢያደርግ ፣ በተለያዩ ሰዎች ( ማለትም በ « ሀ » እና በ « ለ » ) ላይ ፣ እንደ ተራ ቀደሙ ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 544ን እና 618ን በመተላለፍ ፣ የተለያየ ባህርይ ያላቸው ተደራራቢ የወንጀል ድርጊቶችን ( ማለትም የእጅ እልፊትና የሴሰኝነት ስራን ) ይፈጽማል ።

በግዙፋዊ መደራረብ ጉዳዮች የተፈጸሙት የወንጀል ድርጊቶች ሁሉ ፣ አንድን የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ድንጋጌ የሚጥሱ ሊሆኑም ይችላሉ ። ለምሳሌ ፣ « ወ » ከ « ተ » ላይ በተደጋጋሚ[2] ዕቃዎች ቢሰርቅ ፣ ወይም ከ « ሀ » እና ከ « ለ » ሚስቶች ጋር የሩካቤ ስጋ ግንኙነት ቢያደርግ ፣ የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ይኖራል ። በሁለቱም ሁኔታዎች የተፈጸሙት ተከታታይ የወንጀል ድርጊቶች አንድን የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ድንጋጌ ፣ ማለትም በመጀመሪያው ሁኔታ ቁጥር 630ን ፣ በኋለኛው

ሁኔታ ደግሞ ቁጥር 618ን ፣ የሚጥሱ ናቸው ። በመጀመሪያው ሁኔታ ተደራራቢ የወንጀል ድርጊቶቹ የተፈጸሙት በአንድ ሰው ( ማለትም በ « ተ » ) ላይ ሲሆን ፣ በሁለተኛው ሁኔታ ግን በተለያዩ ሰዎች ( ማለትም በ « ሀ » እና በ « ለ » ) ላይ ነው ። [3]

አንድ ወንጀለኛ አንድ ድርጊትን ብቻ በመፈጸም የተለያየ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ድንጋጌዎችን ተላልፎ በሚገኝበት ጊዜም መደራረብ ይኖራል ። ይህ ዓይነቱ መደራረብ « ጣምራዊ መደራረብ » በመባል ይታወቃል ።

በጣምራዊ መደራረብ ጉዳዮች የወንጀለኛው አንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ በርካታ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ድንጋጌዎችን የሚተላለፍ ይሆናል ። ለምሳሌ « ወ » « ሀ » ን ለመግደል በማቀድ በእኩለ ሌሊት « ሀ » ድብን ያለ እንቅልፍ ይዞት ሳለ ቤቱን ቢያቃጥልና ፣ በተነሳውም ቃጠሎ ሳቢያ « ሀ » እና ፣ ስለመኖርዋ « ወ » ሳያውቅ ከ « ሀ » ጋራ አብራው ተኝታ የነበረችው የ « ሀ » ፍቅረኛ ከባድ የአካል ጉዳት ቢደርስባቸው ፣ የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ይኖራል ። በዚህ ሁኔታ « ወ » አንድ ድርጊት ብቻ ፈጽሟል ፤ ሆኖም ይህ አንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ ሁለት የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ድንጋጌዎችን ፣ ማለትም ቁጥር 488ን እና 27/522ን ይተላለፋል ።

ከፍ ብሎ በተገለጸው አኳኋን አንድ ሰው ተደራራቢ የወንጀል ድርጊቶችን ቢፈጽም እንዴት መከሰስና መቀጣት ይኖርበታል ?

በፖሊስ የተደረገው ምርመራ አንድ ተከሳሽ ተደራራቢ ወንጀሎች መፈጸሙን በሚያሳይበት ጊዜ ፣ አቃቤ ህጉ የተለያዩ ክሶችን የያዘ አንድ የክስ ማመልከቻ ማዘጋጀት እንደሚገባው እና ፣ የክሱ ማመልከቻም እየአንዳንዱን ክስ በተናጠል መግለጽ እንደሚኖርበት ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓቱ ይደነግጋል ። [4] ተከሳሹ መከላከያውን በማቅረብ እረገድ ችግር የሚያመጣበት መስሎ ካልታየ በቀርም ፣ ( በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ክሶቹ ለየብቻ እንዲታዩ ፍ/ቤቱ ማዘዝ ይኖርበታል ) ሁሉም ክሶች በአንድነት ይታያሉ ። [5]

ሁሉም ክሶች በአንድነት ከታዩ ፣ ተከሳሹ በሁሉም ወይም በከፊሉ ክሶች ጥፋተኛ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ ፣ ለተፈጸሙት ተደራራቢ የወንጀል ድርጊቶች ቅጣት መወሰን ለፍ/ቤቱ አስቸጋሪ አይሆንበትም ። ይሁን እንጂ ፣ ክሶቹ በተለያዩ ፍ/ቤቶች ወይንም በተለያዩ የአንድ ፍ/ቤት ችሎቶች የሚታዩ ከሆነ ፣ ችግር ይፈጠራል ። ችግሩ የሚፈጠርበትም ምክንያት ፣ የእኛ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርዓት በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ የመጨረሻውን ቅጣት የሚወስነው የትኛው ፍ/ቤት ወይንም ችሎት እንደሆነ ጭርሱኑ ስለማይናገር ነው ። [6]

በአጠቃላይ አነጋገር ፣ ከአንድ በላይ የሆኑ ቅጣቶች የተወሰኑባቸው ተደራራቢ የወንጀል ድርጊቶች ጉዳይ ሲያጋጥም ፣ ቅጣቱን ለመቁረጥ ልዩ ልዩ ዘዴዎች በሥራ ላይ ውለዋል ። እነዚህም ፣ የማዳመር ፣ የማጠቃለል ፣ እና የማክበድ ዘዴዎች ናቸው ።

በአንዳንድ ሀገሮች [7] ፍ/ቤቱ ጥፋተኛነት በተረጋገጠባቸው ተነጣጥለው ለየብቻ በቀረቡ ክሶች ፣ ወይም በአንድ ክስ ማመልከቻ ላይ ለየብቻ ተገልጸው በቀረቡ ክሶች ላይ የተዳመረ ቅጣት የመወሰን ሥልጣን አለው ። በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ለአንዱ ወንጀል የተቆረጠው የእስራት ዘመን ሲፈጸም ፣ ለሌላው ወንጀል የተቆረጠው የእስራት ዘመን መቆጠር ይጀምራል ። በዚህ የቅጣት አወሳሰን ስልት መሠረት አንድ ተከሳሽ ፣ እንበል በስርቆት ፣ በእሳት ቃጠሎ ፣ በኃይል የሩካቤ ስጋ ግንኙነት በማድረግ ፣ የአካል ጉዳት በማድረስ ፣ እና በውንብድና ተግባር

ጥፋተኛ ሆኖ ፣ በእያንዳንዱ ወንጀል የተወሰነ የእስራት ዘመን ፣ እንበል ለስርቆቱ ሶስት ዓመት ፣ ለእሳት ቃጠሎው ስምንት ዓመት ፣ በኃይል ላደረገው የሩካቤ ስጋ ግንኙነት ሰባት ዓመት ፣ ለአደረሰው የአካል ጉዳት ሁለት ዓመት ፣ እንዲሁም ለፈጸመው የውንብድና ተግባር አስር ዓመት ቢፈረድበት ፣ ተዳምሮ ለሰላሳ ዓመት እንዲታሰር ይደረጋል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ፣ አንዳንድ ህጎች [8] « የማጠቃለል » ዘዴን ይከተላሉ ። በዚህ ስልት መሠረት ፣ ለከፍተኛው ወንጀል የተወሰነው ቅጣት ፣ አነስተኛ ለሆኑት ወንጀሎች የሚወሰኑትን ቅጣቶች ያጠቃልላል ። ከላይ በሰጠነው ምሳሌ ፣ ተከሳሹ ከፈጸማቸው የወንጀል ድርጊቶች ሁሉ ወንበዴነት ከፍተኛው ወንጀል ነው ብንል ፣ ( በእኛ ህግ ከፍተኛው ነው ) ለወንበዴነት በፍ/ቤቱ የተወሰነው ቅጣት ማለትም የአስር ዓመቱ የእስራት ዘመን ፣ ለሌሎቹ ወንጀሎች የሚወሰኑትን ቅጣቶች ሁሉ ያጠቃልላል ።

ይሁን እንጂ ፣ እነዚህ ሁለት የቅጣት አወሳሰን ዘዴዎች ደካማ ጐኖች ያሏቸው ይመስላል ። አንድ የእስራት ዘመን ሲያልቅ ፣ ሌላው የእስራት ዘመን የሚጀምርበት የማዳመር ዘዴ ፣ ቅጣት ያለውን ጥፋተኛውን እርሞ ወደ ህብረተሰቡ የመመለስ ዓላማ ያጨናግፋል ። ተከሳሹ ከሚያስፈልገው በላይ ለረዥም ጊዜ ታስሮ [9] ስለሚቆይ ፣ ይህ አሰራር ወንጀለኛውን እርሞና አሻሽሎ ወደ ህብረተሰቡ ለመመለስ የሚደረገውን ማንኛውንም እቅድ የሚያከሽፍ ይሆናል ። እንዲህ ዓይነቶቹ ልዩ እርዝማኔ ያላቸው የማዳመር ቅጣቶች «የማይገቡ ወይም ፍትሕ አልባ » በመሆናቸው ሳይሆን ፣ « በጊዜው ካሉት የሰብአዊ ክብር መለኪያዎች » ጋራ የሚስማሙ ባለመሆናቸው ምክንያት ፣ አንድ ጸሐፊ « ኢሰብአዊ » በማለት ገልጿቸዋል ። [10] በእርግጥም የጥፋተኝነት ፍርድ የተሰጠበት አንድ ተከሳሽ ለመቶ ዓመት ታስሮ ይቆይ ማለት የማይሆን ነገር ነው ።

የማጠቃለል ዘዴም ለችግሩ እርኪ የሆነ መፍትሄ አይመስልም ። ይህ ዘዴ አሁንም ቢሆን በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያላቸውን የመከላከልንና የመበቀልን የቅጣት ዓላማዎች ሊያሟላ አይችልም ፤ ምንም እንኳን እነዚህ ጽንሰ ሃሳቦች « ከጊዜው የሰብአዊ ክብር መለኪያዎች » ጋራ የሚስማሙ መስለው ባይታዩም ። የማጠቃለል ዘዴ አንድ ወይም ከአንድ የበለጡ የወንጀል ተግባሮች ቅጣት ሳይወሰንባቸው እንዲቀሩ ስለሚያደርግ ፣ ብዙውን ጊዜ ቀለል ያሉ ቅጣቶችን የሚያስከትል ይሆናል ።

ጥፋተኛው የወንጀል ድርጊቶችን ለመፈጸም ያለው አደገኛ ዝንባሌ ሲታይም ፣ ይህ አሰራር ወደፊት ሌሎች ተመሳሳይ የወንጀል ድርጊቶችን ከመፈጸም የሚያግደው አይሆንም ። በተጨማሪም ፣ ጥፋተኛው የሚገባውን ቅጣት እንዳላገኘ ሆኖ ስለሚታይ ፣ ህብረተሰቡ ስለፍትህ ያለው ስሜት ላይረካ ይችላል ። ቅጣት ካለው ፣ ጥፋተኛውን እርሞ ወደ ህብረተሰቡ የመመለስ ዓላማ አንጻር ቢታይ እንኳን ፣ ( ይህ ከሁሉም እጅግ ከፍተኛው ዓላማ ነው ) ሁኔታው ጥፋተኛውን ለማረም ከተለመደው ጊዜ እረዘም ያለ የሚጠይቅ በሚሆንበት ወቅት ፣ እንዲህ ያለው አጭር የእስራት ዘመን ጥፋተኛው አስፈላጊውን እርማት እንዲያገኝ ለማድረግ በቂ ላይሆን ይችላል ።

ሁለቱንም ዘዴዎች ለማስታረቅ የሚሞክር መስሎ የሚታየው ሶስተኛው ዘዴ የማክበድ ስልት ነው ። በዚህ የቅጣት አወሳሰን ስልት መሠረት ፣ የእስራት ዘመናትን ከመቆለል ወይም ለአንዳንድ ወንጀሎች በህግ የተወሰኑትን ቅጣቶች ሙሉ በሙሉ ከማስቀረት ፋንታ ፣ በመጀመሪያ ከሁሉም ይልቅ ከባድ ለሆነው

ወንጀል የተደነገገው ቅጣት ይቆረጥና አግባብ ባላቸው ሁኔታዎች ብቻ ቅጣቱ እንዲከብድ ይደረጋል ። ይሁን እንጂ ፥ ቅጣቱ የሚከብድበት መጠን የተገደበ ነው ። ፍ/ቤቱ እንዲያከብራቸው የሚገደደው የተለመዱት ገደቦችም ሁለት ናቸው።

የመጀመሪያው ገደብ ፍ/ቤቱ ከሁሉ ይልቅ ከባድ ለሆነው ወንጀል የተወሰነውን « መሠረታዊ ቅጣት » ከግማሽ በላይ ማለፍ እንደሌለበት የሚከለክለው ነው ። ይህም ማለት ፥ ለምሳሌ ፥ ከሁሉ ይልቅ ከባድ ለሆነው ወንጀል የተወሰነው « መሠረታዊ ቅጣት » የሰባት ዓመት የእስራት ዘመን ቢሆን ፥ ፍ/ቤቱ ለተደራራቢ ወንጀሎቹ ቅጣቱን በሚያከብድበት ጊዜ ፤ ይህን ቅጣት ከግማሽ ፥ ማለትም ከሶስት ዓመት ተኩል ፥ በላይ ማስበለጥ አይችልም ።

ሁለተኛው ገደብ ደግሞ ፥ ፍ/ቤቱ « መሠረታዊውን ቅጣት » በግማሽ ያህል ሲያሳድግ ፥ ለሚወሰነው የቅጣት ዓይነት በህግ ከተወሰነው ከጠቅላላው ከፍተኛ ጊዜ እንዳያልፍ የሚከለክለው ነው ። በላይኛው ምሳሌ ፥ ለቅጣቱ ዓይነት የተወሰነው ጠቅላላ ከፍተኛ ጊዜ አስር ዓመት ቢሆን ፥ ፍ/ቤቱ ከዚህ ወሰን ሊያልፍ አይችልም ። በመሆኑም ፥ መሠረታዊውን ቅጣት በሶስት ዓመት እንጂ በሶስት ዓመት ተኩል ለማሳደግ አይችልም ።

በእኛ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ታሪክ ውስጥ ፥ የ1923ቱ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ በስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ፤ የማዳመርና የማጠቃለል ዘዴዎች ይሠራባቸው ነበር ።[11] በ1949ኙ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ( አሁንም በስራ ላይ ነው ) የማጠቃለል ዘዴ ሙሉ በሙሉ እንዲቀር ተደርጐ ፥ በምትኩ የተደራራቢ ወንጀሎችን ቅጣት ለመወሰን የማክበድ ዘዴ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል ። የማዳመር ዘዴ ግን ፥ ለተደራራቢ የደንብ መተላለፍ ጥፋቶች ተፈጻሚ የሚሆነውን ቅጣት ለመወሰን አሁንም ይሠራበታል ።[12]

ነጻነትን የሚያሳጡ ቅጣቶችን ማክበድን በሚመለከት የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 189 የሚከተለውን ይደነግጋል ፤

/1/ ግዙፍ[13] የሆነ የጥፋት መደራረብ ጉዳይ ባጋጠመ ጊዜ ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ለማክበድ የወንጀለኛውን ተግባር ከባድነት እንደመጠኑ በመገመት ቅጣቱን የሚቆርጠው ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ጠቅላላ ድንጋጌዎች ውስጥ ያሉትን ደንቦች በመከተል ነው (ቁ 82)

/ሀ/ ተደራራቢ ከሆኑት ነጻነትን ከሚያሳጡ ጥፋቶች ባንደኛው ምክንያት የሞት ቅጣት የሚወሰን ሲሆን ፥ ይህ ውሳኔ ስለ ሌሎቹ ተደራራቢ ጥፋቶች የሚወሰነውን ቅጣት ሁሉ ደርቦ ይይዛል ።

/ለ/ ነጻነትን የሚያሳጡ ቅጣቶች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ ፥ ፍ/ቤቱ ቅጣትን የሚወስነው ከሁሉ ይልቅ ከባድ ለሆነው ጥፋት የተወሰነውን ቅጣት ነው ። እንዲህም ሲሆን ፥ በተደራራቢነት በተፈጸሙት ጥፋቶች መጠን ፥ ወይም በተሠራው ህግ ድንጋጌዎች መሠረት ፥ ቅጣቱን ማሳደግ አለበት ። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ፥ መሠረት አድርጎ ለያዘው ጥፋት በተወሰነው ከፍተኛ የቅጣት ዘመን ላይ የዚሁ የቅጣት ዘመን አጋማሽ እስኪሆነው ድረስ በመጨመር ማሳደግ ይችላል ። ቢሆንም ፤ በሚወሰነው ቅጣት ዓይነት በህጉ ከተወሰነው ከጠቅላላው ከፍተኛ ጊዜ አልፎ ለመቅጣት አይችልም ።

በዚህ ቁጥር በንዑስ ቁጥር /1/ መሠረት ፣ አንድ ተከሳሽ ተደራራቢ የወንጀል ድርጊቶችን በመፈጸሙ ጥፋተኝነቱ ቢረጋገጥና ፣ ከተደራራቢ የወንጀል ድርጊቶቹ መካከል ለአንደኛው የተደነገገው ቅጣት ሞት ቢሆን[14] ፣ ፍ/ቤቱ የተከሳሹን ጥፋት ከባድነት እግምት ውስጥ በሚያስገባበት ጊዜ ፣ የሞት ቅጣት ይገባዋል የሚል አስተሳሰብ ቢኖረው ፣ ማናቸውንም ሌሎች ነጻነትን የሚያሳጡ ቅጣቶችን ደርቦ የሚይዘውን ይህን ቅጣት ሊወስንበት ይችላል ።

በዚህም መሠረት ፣ « ወ » « ተ » ን በኃይል በሩካቤ ሥጋ ቢገናኛትና ፣ ቀጥሎም ጭካኔ በተሞላበት አኳኋን ቢገድላት ፣ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 589 እና 522 ላይ የተመሠረተ ተደራራቢ የወንጀል ክስ ይቀርብበታል ። በ « ወ » ከተፈጸሙት የወንጀል ድርጊቶች አንደኛው ፣ ማለትም የግፍ አገዳደል ፣ የሞት ቅጣት የሚያስከትል በመሆኑ ፣ ፍ/ቤቱ ይህ ቅጣት ይገባዋል ብሎ ካሰበ ፣ የሞት ቅጣት ሊወስንበት ይችላል ። [15] ይህም ፣ በኃይል ለሚፈጸም የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት የተደነገገውን ቅጣት ደርቦ ይይዛል ። ቁጻዮቹ በቁጥር 189 /1/ /ሀ/ የሚሸፈኑ ሲሆን ፣ ፍ/ቤቶቻችን ቅጣቶችን ለመወሰን ችግር አይገጥማቸውም ይሆናል ። ቅጣቱን በቁጥር 189 /1/ /ለ/ መሠረት በሚወስኑበት ጊዜ ግን ፣ ችግር ሊገጥማቸው ይችላል ። ችግሩም በእንግሊዝኛው ቅጅ ውስጥ « መሠረታዊ ቅጣት » ከሚለው አባባል ትርጉም ጋራ የተያያዘ ነው ።

በቁጥር 189 /1/ /ለ/ መሠረት ፣ ነፃነትን የሚያሳጡ በርካታ ቅጣቶች ተደራርበው በተገኙ ጊዜ ፣ ፍ/ቤቱ ከሁሉም ይልቅ ከባድ ለሆነው ወንጀል ተገቢውን ቅጣት ይወስንና ፣ ተደራራቢ ወንጀሎቹን . . . እግምት ውስጥ በማስገባት ፣ የእሥራት ዘመኑን ያራዝመዋል ። የቅጣቱን ዘመን በሚያራዝምበት ጊዜም ፣ « ፍ/ቤቱ አግባብ ሆኖ ካገኘው ለቅጣቱ ዓይነት በህግ ከተደነገገው ከጠቅላላው ከፍተኛ ጊዜ ሳያልፍ <u>የመሠረታዊውን ቅጣት</u> በግማሽ የሚበልጥ ቅጣት ለመወሰን ይችላል» [16] ( ስርዝ የተጨመረ) ።

በእንግሊዝኛው ቅጂ « መሠረታዊ ቅጣት » ( ቤዚክ ፔናልቲ) የሚለው ቃል ፣ « ከሁሉ ይልቅ ከባድ ለሆነው ጥፋት የተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት » ተብሎ ወደ አማርኛ ተተርጉሟል ። በእንግሊዝኛው ቅጅ ውስጥ ይህ አባባል አሻሚ መስሎ ይታያል ። ዳሩ ግን ፣ ከአማርኛው ቅጅና ከዚህ አንቀጽ [17] ምንጮች አኳያ ሲታይ ፣ እነዚህ ቃላት በፍ/ቤት የሚወሰነውን ቅጣት ሳይሆን ፣ በህጉ ከሁሉ ይልቅ ከባድ ለሆነው ጥፋት የተደነገገውን ከፍተኛ ቅጣት እንደሚያመለክቱ አያጠራጥርም ። በእንሊዝኛውና በፈረንሳይኛው ቅጅዎች ላይ የበላይነት ማግኘት ያለበት የአማርኛው ቅጅ ፣ « ከሁሉ ይልቅ ከባድ ለሆነው ጥፋት የተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት » የሚል አነጋገር በመጠቀም ፣ አሻሚ የሆነውን ሁኔታ አስወግዶታል ። የቅጣቶችን ከፍተኛና ዝቅተኛ ገደቦች የሚደነግገው ህግ እንደሆነና ፣ ፍ/ቤቶችም በነኝሁ በተወሰኑት ገደቦች ውስጥ ቅጣቱን የመወሰን ሥልጣን እንዳላቸው ግልጽ ነው ። ለምሳሌ ፣ ለተራ ነፍስ ግድያ በህግ የተደነገገው ቅጣት ከአምስት እስከ ሃያ ዓመት የሚደርስ ጽኑ እስራት ነው ። ለወንጀሉ የተደነገገው ዝቅተኛ የቅጣት ዘመን አምስት ዓመት ሲሆን ፣ ከፍተኛው ደግሞ ሃያ ዓመት ነው ። ፍ/ቤት የአንድን ወንጀል ዝቅተኛና ከፍተኛ የቅጣት ዘመን ለመከለል ሥልጣን የለውም ። እነዚህ በህግ የተወሰኑ ናቸው ።

በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1569/74 አብላጫው ድምጽ [18] መሠረታዊ ቅጣት የሚለው አባባል ፍ/ቤቱ ከሁሉ ይልቅ ከባድ ለሆነው ወንጀል የሚወስ

ነው ቅጣት ነው ብሏል ። ዳሩ ግን ፣ ይህ ውሳኔ ፣ በተለይ ፍ/ቤቱ ሊከተለው ይገባው ከነበረው ከአማርኛው ቅጅ ግልጽ ድንጋጌ አኳያ ሲታይ ፣ ስህተት ነው ።

በተደራራቢ የወንጀል ድርጊቶች ጉዳይ፣ ፍ/ቤቱ ቅጣቱ በህግ ከሁሉ ይልቅ ከባድ ለሆነው ጥፋት ከተደነገገው ከፍተኛ የቅጣት ዘመን በላይ መራዘም አለበት ብሎ ካሰበ ፣ ጭማሪው የቅጣቱን ግማሽ እስካላለፈ ድረስ ፣ እና ለቅጣቱ ዓይነት በህግ ከተደነገገው ከጠቅላላው ከፍተኛ ዘመን እስካልበለጠ ድረስ ፣ ቅጣቱን ለማራዘም ይችላል ።

ይህን በምሳሌ እንግለጽ ። « ወ » በቃጠሎ / ቁ. 488/ ፣ በውንብድና / ቁ.636 / ፣ እና በተራ ነፍስ ግድያ / ቁ .523 / ወንጀሎች ተከሶ ፣ በመጀመሪያዎቹ ሁለት የወንጀል ድርጊቶች ጥፋተኛ ሆኖ ተገኘ እንበል ። « ወ » ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘባቸው ሁለት የወንጀል ድርጊቶች ከባዱ ውንብድና ነው ።[19] እንግዲህ ፍ/ቤቱ ተደራራቢ ለሆኑት ወንጀሎች ቅጣት ሲወስን ፣ በመጀመሪያ የውንብድናውን ወንጀል ብቻ ይወስድና ፣ « ወ » በዚህ ወንጀል ብቻ ተከስሶ ቢሆን ኖሮ ይፈርድበት የነበረውን ቅጣት ይወስናል ። ቀጥሎም ፣ ሌላውን ወንጀል እግምት ውስጥ በማስገባት ፣ የቅጣቱን ዘመን ያራዝማል ። « ወ » ለፈጸመው የውንብድና ወንጀል የአስር ዓመት ጽኑ እሥራት ቅጣት ይገባዋል ብሎ ፍ/ቤቱ ከወሰነ ፣ ሌላውን ወንጀል እግምት ውስጥ በማስገባት ፣ ይህንን የቅጣት ዘመን ማራዘም ይኖርበታል ። የቅጣቱን ዘመን ሲያራዝምም ፣ ፍ/ቤቱ ለውንብድና በህግ የተደነገገውን የእስራት ዘመን ፣ ማለትም የአስራ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት ፣ በመወሰን ብቻ ሊታቀብ ፣ ወይም ይህን መሠረታዊ የቅጣት ዘመን እስከ አጋማሹ ፣ ማለትም ሰባት ዓመት ተኩል ፣ ድረስ በአስር ዓመቱ ላይ በመደመር ሊያሳድገውና ፣ በ « ወ » ላይ የአስራ ሰባት ዓመት ተኩል ጽኑ እስራት ሊወስንበት ይችላል ። ፍ/ቤቱ መጀመሪያውኑ ለ « ወ » የሚገባው ቅጣት ለውንብድና የተደነገገው ከፍተኛው የእስራት ዘመን ነው ፤ የሚል ቢሆን ግን ፣ ሌላውን ወንጀል ( ማለትም ቃጠሎን ) እግምት ውስጥ በማስገባት ፣ ይህን በህግ የተደነገገውን ከፍተኛ ቅጣት እስከ አጋማሹ ድረስ በማሳደግ ፣ « ወ » በሃያ ሁለት ዓመት ተኩል ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሊወስን ይችላል ። ይሁን እንጂ ፣ ፍ/ቤቱ በምንም ዓይነት ሁኔታ ከዚህ ገደብ ማለፍ አይችልም ።

በላይኛው ምሳሌ « ወ » በተከሰሰባቸው የወንጀል ድርጊቶች ሁሉ ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ ፣ ፍ/ቤቱ በመጀመሪያ ለግድያው ወንጀል ቅጣቱን ይወስናል ። ቀጥሎም ሌሎቹን የወንጀል ድርጊቶች ( ማለትም ቃጠሎንና ውንብድናን ) እግምት ውስጥ በማስገባት ፣ የቅጣቱን ዘመን ያራዝመዋል ። ዳሩ ግን ፣ እዚህ በተገለጸው በዚህ ልዩ የእንዲህ ቢሆን ሁኔታ ፣ ፍ/ቤቱ የመሠረታዊውን ቅጣት አጋማሽ ለመጨመር አይችልም ። ይህን ቢያደርግ ግን ፣ ለዚህ ዓይነቱ ጥፋት በህግ ከተደነገገው ከጠቅላላው ከፍተኛ የቅጣት ዘመን ፣ ማለትም ከሃያ አምስት ዓመት ፣ አልፎ ይሄዳል ።[20] ስለዚህ ፣ ፍ/ቤቱ ከዚህ ከጠቅላላው ከፍተኛ የቅጣት ዘመን እንዳያልፍ የተከለከለ ስለሆነ ፣ በመሠረታዊው ቅጣት ላይ አምስት ዓመት ብቻ በመጨመር ፣ « ወ » በሃያ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ሊወስንበት ይችላል ።

እንግዲህ ፣ ይህ ትክክል የሚሆነው ፣ ተከሳሹ በአንድ ፍ/ቤት በሚከሰስበትና ተደራራቢ ወንጀሎቹ በሙሉ በዚያው ፍ/ቤት በሚታዩበት ጊዜ ነው ። ዳሩ ግን የተለያዩ የክስ ማመልከቻዎች ተዘጋጅተው ለተለያዩ ፍ/ቤቶች ወይንም ለተለያዩ የአንድ ፍ/ቤት ችሎቶች የሚቀርቡበት ጊዜ ሊኖር ይችላል ። ይህ አንድም በስህተት ፣ ወይንም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 116 /2 /

መሠረት ሊፈጸም የሚችል ነው ። በመሆኑም እያንዳንዱ ፍ/ቤት ፣ ወይንም ችሎት ተከሳሹን ጥፋተኛ በማድረግ ለእያንዳንዱ ወንጀል የተለያየ ቅጣት በሚወስንበት ጊዜ ፣ የአፈጻጸም ችግር ሊፈጠር ይችላል ።

ጉዳዩ ከፍርድ በፊት ስለተፈጸመ ተደራራቢ ወንጀል ከሆነ ፣ ( ማለትም ከአንድ ወይም በርካታ ከሆኑ ሌሎች ወንጀሎች ጋራ በተደራራቢነት የተፈፀመ አንድ ወንጀል ፣ የተባሉት ሌሎች ወንጀሎች ፍርድ ከተሰጠባቸው በኋላ ዘግይቶ የተገለጸ እንደሆን ) የወንጀል ድርጊቶቹ በአንድነት ታይተው ቢሆን ኖሮ በወንጀለኛው ላይ ከሚወሰነው ቅጣት የበለጠ ከባድ ቅጣት እንዳይደርስበት በማድረግ ፣ ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ፣ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 189 የተደነገጉትን መሠረተ ሃሳቦች በመከተል ፣ ይወስናል ።[21] በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ፣ አዲሱ ቅጣት ያለፉትን ቅጣቶች እግምት ውስጥ በማስገባት ይወሰንና ፣ ቀደም ሲል ከተወሰነው ቅጣት ጋራ ይታሰባል ።[22] በሌላ አነጋገር ፣ የአዲሱ ቅጣት ዘመን ፣ ቀደም ሲል የተወሰነው ቅጣት መቆጠር በጀመረበት ጊዜ አብሮ መታሰብ እንደ ጀመረ ይገመታል ። ለምሳሌ ፣ « ወ » የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 656ን በመተላለፍ የማታለል ወንጀል በመፈጸሙ ፣ ጥፋተኛ ተብሎ በሁለት ዓመት እሥራት እንዲቀጣ ከተፈረደበት በኋላ ፣ ከዚህ ፍርድ በፊት ሌላም የማታለል ወንጀል መፈጸሙ ዘግይቶ ቢደረስበት ፣ ፍርድ ቤቱ ሁለቱ ወንጀሎች በአንድነት ታይተው ቢሆን ኖሮ ይወስን ከነበረው ቅጣት እኩል የሆነ አንድ አጠቃላይ ቅጣት ይወስናል ። ፍርድ ቤቱ እነዚህን ሁኔታዎች አውቆ ቢሆን ኖሮ ፣ ለሁለቱም ወንጀሎች የሶስት ዓመት ጽኑ እሥራት ቅጣት ይወስን ከነበረ ፣ አሁን ይህንኑ ቅጣት ይወስናል ። ይህ አዲሱ ቅጣትም ፣ የመጀመሪያው የሁለት ዓመት ቅጣት መቆጠር በጀመረበት ቀን መታሰብ እንደጀመረ ይገመታል ።

ይሁን እንጂ ፣ ተከሳሹ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ፣ ወይም በተለያዩ የአንድ ፍርድ ቤት ችሎቶች ሲፈረድበትና ፣ የተለያዩ የእሥራት ዘመናት ሲወሰንበት ፣ የአፈጻጸም ችግር ይፈጠራል ። እንዲህ ያሉት ቅጣቶች እንዴት መፈጸም ይገባቸዋል ? ጐን ለጐን መፈጸም ይኖርባቸዋል ወይስ በተከታታይ ? ወይስ ፍርድ ቤቱ ፣ በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ፣ ሁሉንም ተደራራቢ ወንጀሎች እግምት ውስጥ በማስገባትና ቀደም ሲል የተወሰኑትን ቅጣቶች መሠረት አድርጐ በመያዝ ፣ አንድ አጠቃላይ ቅጣት መወሰን ይገባዋል ? የሚገባው ከሆነስ ፣ ቀደም ሲል ያልተፈረደ አዲስ ቅጣት እንደመወሰን የሚታይና ፣ ለአንድ ጥፋት ሁለት ጊዜ መከሰስና መቀጣት የለም ፤ የሚለውን መሠረተ ሀሳብ መጻረር ይሆናልን ?

እነኝህን ጥያቄዎች በሚመለከት ፣ የኮመን ሎ አቋም ፣ ቅጣቶች በተከታታይ እንደሚፈጸሙ ፍርድ ቤቶቹ ካልገለጹ በቀር ፣ ጐን ለጐን መፈጸም ይኖርባቸዋል ፤ የሚል ነው ። ተነጣጥለው የተወሰኑት ቅጣቶች አንዴ የመጨረሻ ከሆኑ ፣ ፍርድ ቤቶቹ ቅጣቱን በሚወስኑበት ወቅት ፣ ስለወንጀሎቹ ተደራራቢነት ማወቅ አለማወቃቸው ምንም ዓይነት ልዩነት የሚያመጣ መስሎ አይታይም ።

በሌላ በኩል ፣ ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥም ፣ የወንጀሎቹን ተደራራቢነት እግምት ውስጥ በማስገባት ፣ ከፍርድ በፊት ለተፈጸመና ዘግይቶ ለታወቀ ተደራራቢ ወንጀል ቅጣት በሚቆረጥበት አኳኋን ፣ አንድ አዲስ ቅጣት እንዲቆረጥ የሚደነግጉ ሌሎች ሕጐች አሉ ።[23]

ይሁን እንጂ ፣ የእኛን ሕግ ጨምሮ ፣ ለዚህ ዓይነቱ ችግር ግልጽ መፍትሄ የማይሰጡ ሌሎች ብዙ ሕጐች አሉ ። ታዲያ እንዲህ ያሉ ግልጽ ድንጋጌዎች በሌ

ሉበት ሁኔታ የተፈጠረውን ቀዳዳ በማመሳሰል የዳኝነት አተረጓጐም ዘዴ መሸፈኑ አግባብ ይሆናል ።

ለተደራራቢ ወንጀሎች የተለያዩ የመጨረሻ ቅጣቶች በፍርድ ቤቶች ተወስነው ሲገኙ ፣ ከፍርድ በፊት ለተፈጸመና ዘግይቶ ለታወቀ ተደራራቢ ወንጀል ቅጣት በሚወሰንበት አኳኋን ( ማለትም ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች አንድ ላይ ሲታዩ ቅጣቱ በሚወሰን በት ዓይነት ) ተደራራቢ ወንጀሎቹን እግምት ውስጥ በማስገባት አንድ አዲስ ቅጣት ይቆረጣል ፤ በማለት የስዊድን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ምዕራፍ 34 ክፍል 10 አንቀጽ ሁለት እና የሪፓብሊክ ቻይና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 53 ይደነግጋሉ ። እነዚህ ሁለት የወንጀለኛ መቅጫ ድንጋጌዎች፡ወንጀለኛውን ከከባድ ቅጣት ነጻ አያደርጉትም ። ሁሉም ወንጀሎች በአንድነት ቢታዩ ኖሮ ፣ ይቆረጥበት ከነበረው ለበለጠ ቅጣትም ፣ አያጋልጡትም ።

በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ፣ ወንጀለኛው ከከበደ ቅጣት ነጻ የሚደረግበት አንዳች አጥጋቢ ምክንያት ያለ አይመስልም ። ሁሉም ተደራራቢ ወንጀሎች በአንድነት ታይተው ቢሆን ኖሮ ፣ ወንጀለኛው ከበድ ያለ ቅጣት ይፈረድበት ነበር ። በተመሳሳይ ሁኔታ ፣ ወንጀለኛው ለሌላው ወንጀል ( ለሌሎቹ ወንጀሎች ) [24] ቅጣት ከተፈረደበት በኋላ ፣ ተደራራቢ ከሆኑት ወንጀሎች መካከል አንደኛው ዘግይቶ ቢገለጽ ኖሮ ፣ ቀድሞ የተወሰነውን ቅጣት እግምት ውስጥ በማስገባት ፣ አንድ አዲስ ቅጣት ይወሰን ነበር ። የሕጉ አቋም ይህ ከሆነ ፣ ከፍርድ በፊት ለተፈጸመና ዘግይቶ ለታወቀ ተደራራቢ ወንጀል ቅጣት በሚወሰንበት ሁኔታና ፣ በስህተት ወይም የተፈጸሙትን ወንጀሎች ተደራራቢነት ባለማወቅ የተለያዩ የመጨረሻ ቅጣቶች በተወሰኑበት ሁኔታ መካከል ልዩነት ሊኖር ይገባልን ?

የዚህ ትችት አቅራቢ ሁሉም ወንጀሎች በአንድነት ታይተው ቢሆን ኖሮ ወንጀለኛው መቀጣት ከነበረበት ያነሰ ወይም የበለጠ ቅጣት ለመወሰን ምክንያት የሚሆን አሳማኝ ልዩነት ፣ በሁለቱ ሁኔታዎች መካከል አያይም ። በመሆኑም ፣ በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ፣ ፍርድ ቤቶቻችን ቀደም ሲል የተቆረጠውን ቅጣት ( የተቆረጡትን ቅጣቶች ) እግምት ውስጥ በማስገባት ፣ አንድ አዲስ ቅጣት ሊቆርጡ ይገባቸዋል ። አዲሱ ቅጣትም ፣ ቀደም ሲል የተቆረጠው ቅጣት ( የተቆረጡት ቅጣቶች ) መታሰብ ከጀመረበት ( ከጀመሩበት ) ቀን አንስቶ መቆጠር ይኖርበታል ።

ስለዚህ ፣ በወንጀል ይግባኝ መዝገበ ቁጥር 1569/74 ተነስቶ የነበረውን ይህንን ጭብጥ በሚመለከት ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 191 በማመሳሰል የአተረጓጐም ዘዴ ተፈፃሚነት ሊኖረው ይገባል ፤ በማለት አብላጫው ድምጽ የወሰደው አቋም ትክክለኛ ነው ።

በሌላ በኩል ፣ አነስተኛው ድምጽ በእንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ አዲስ ቅጣት መወሰን ፣ አንድ ሰው በአንድ ወንጀል ሁለት ጊዜ መከሰስ ወይም መቀጣት አይኖርበትም ፤ የሚለውን መሠረተ ሀሳብ እንደሚጻረር አድርጐ ቆጥሮታል ። ዳሩ ግን ፣ ሁሉንም ተደራራቢ ወንጀሎች እግምት ውስጥ የሚያስገባና አጠቃላይ የሆነ አንድ አዲስ ቅጣት መወሰን ፣ እንደምን ይህንን መሠረተ ሀሳብ ሊፃረር እንደሚችል አነስተኛው ድምጽ አላብራራም ።

አንድ ሰው ሁለት ጊዜ አይቀጣም ፣ የሚለው መሠረተ ሀሳብ ተፈፃሚነት የሚኖረው ፣ አንድ ሰው ቀደም ብሎ በተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት ከተፈረደ

በት ወይም ነፃ ከወጣ በኋላ በዚያው የወንጀል ድርጊት እንደገና በሚከሰስበት ሁኔታ ላይ ነው ። ዳሩ ግን ፣ ከፍ ብለን ባነሳናቸው የእንዲህ ቢሆን ሁኔታዎች ጭብጡ ይህ አይደለም ፤ ( በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1569/74ም ቢሆን የተነሳው ጭብጥ ይህ አልነበረም ። ) በነዚህ ሁኔታዎች ፣ የክሱ መሰማትና ጥፋተኝነቱን የማረጋገጡ ተግባር ተከናውኗል ። ለእያንዳንዱ ተደራራቢ የወንጀል ድርጊት የተለያየ ቅጣት የተወሰነ መሆኑም እርግጥ ነው ። ጥያቄው ግን ፣ እንዲህ ያሉት ቅጣቶች አፈፃጸማቸው እንዴት መሆን ይገባዋል ? የሚል ነው ።

የእኛ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፣ ቅጣቶች እንዲዳመሩም ሆነ ለከፍተኛው ወንጀል በተቆረጠው ቅጣት ብቻ እንዲጠቃለሉ አያዝም ። ሕጉ የሚደነግገው ፣ በተደራራቢ ወንጀሎች ጉዳይ ፣ በአንድነትም ሆነ ተነጣጥለው ቢታዩ ፣ ለሁሉም ወንጀሎች አንድ አጠቃላይ ቅጣት ብቻ መቆረጥ እንዳለበት ነው ። በመሆኑም ፣ ፍርድ ቤቶች በማናቸውም ምክንያት የወንጀል ድርጊቶቹን ተደራራቢነት ሳያውቁ ቀርተው ፣ ለእያንዳንዱ ወንጀል የተለያየ ቅጣት ቆርጠው በሚገኙበት ጊዜ ፣ ጥፋተኛው ሁሉም የወንጀል ድርጊቶች በአንድነት ታይተው ቢሆን ኖሮ ሊወሰንበት ከሚገባው ያነሰ ወይም የበለጠ እንዳይቀጣ ፣ ሁሉንም ተደራራቢ ወንጀሎች እግምት ውስጥ የሚያስገባ አንድ አዲስ ቅጣት መቁረጡ ፣ ሕሊናን የማይፃረርና አግባብም ይሆናል ። አዲሱን ቅጣት የመወሰኑ ሥልጣንም ፣ ከሁሉ ይልቅ ከባድ የሆነውን ወንጀል ያየው ፍርድ ቤት ሊሆን ይገባል ።

ይሁን እንጂ ፣ በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1569/74 የተነሳው « ሁለቱ የአሥር ዓመት እሥራት ቅጣቶች እንዴት መፈጸም ነ ለባቸው ? » የሚለው ጭብጥ ቅጣት የማክበድ ጥያቄ ባለመሆኑ ፣ አዲስ ቅጣትን በመወሰን ሊፈታ የሚችል አልነበረም ። አብላጫውም ሆነ አነስተኛው ድምጽ ፣ ይህንን ጭብጥ ቅጣት የማክበድ ጥያቄ አድርገው በማስተናገዳቸው ፣ የዚህ ትችት አቅራቢ ፣ ተሳስተዋል የሚል አስተያየት አለው ።

በከፍተኛው ፍርድ ቤት ሁለት የተለያዩ ክሶች ( ማለትም የወንጀል መዝገብ ቁጥር 27/72 እና 341/72) በይግባኝ ባዩ ላይ ቀርበው ነበር ። በወንጀል መዝገብ ቁጥር 27/72 [25] ይግባኝ ባዩ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/522 /1/ /ሀ/ መሠረት ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ ፣ ምንም እንኳን ለዚህ ክስ የእድሜ ልክ እሥራት ወይም ሞት ሊፈረድበት ይችል የነበረ ቢሆንም ፣ በአሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ተፈርዶበታል ። በወንጀል መዝገብ ቁጥር 341/72 [26] ደግሞ ፣ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 32/1/ /ሀ/ /668/522 /1/ /ሀ/ [27] መሠረት ክስ ቀርቦበት ጥፋተኛ ሆኖ በመገኘቱ ፣ በሞት እንዲቀጣ ተፈርዶበታል ። ይግባኝ ባዩ ሁለቱን ወንጀሎች በአንድ ቀን በሁለት ሰዓት ልዩነት ውስጥ የፈጸማቸው መሆኑንም ፣ ሁለቱ ክሶች ያመለክታሉ ።

በወንጀል መዝገብ ቁጥር 341/72 ፣ የጥፋተኝነት ፍርድና የቅጣት ውሳኔ የተሰጠው ፣ ይግባኝ ባዩ በሌላ ክስ (በወንጀል መዝገብ ቁጥር 27/72 ) በአሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ ከተፈረደበት በኋላ ነው ። ልክ የጥፋተኝነቱ ውሳኔ እንደተሰጠ ፣ ነገር ግን ገና ቅጣቱ ሳይቆረጥ ፣ አቃቤ ሕጉ ይግባኝ ባዩ ሌላም ወንጀል ፈጽሞ በአሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት የተቀጣ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ በመግለጽ ፣ ለሁለተኛው ወንጀል በሕግ የተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት እንዲወሰንበት ጠየቀ ። ይህ ሁኔታ ፣ የከፍተኛው ፍ/ቤት ለሁለተኛው ወንጀል ( በወንጀል መዝገብ ቁጥር 341/72 ለተገለጸው ) ቅጣቱን በወሰነበት ጊዜ ፣ የሁለቱን የወንጀል ድርጊቶች ተደራራቢነት [28] ያውቅ እንደነበር ያሳያል ። ይህም

ማለት ፣ አዲሱ ቅጣት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 191 እና 189/1/ /ሀ/ ድንጋጌዎች መሠረት የተወሰነ ነው ማለት ነው ።

እንግዲህ ፣ ምንም እንኳን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሞት ቅጣት በፈረደበት ጊዜ ሌላውን የወንጀል ድርጊት እንደቅጣት ማክበጃ ምክንያት አድርጎ የወሰደው ለመሆኑ ምንም የገለጸው ነገር ባይኖር ፤ እንደ ቅጣት ማክበጃ ምክንያት አድርጎ ወስዶታል የሚል ግምት መውሰዱ አግባብ ይሆናል። ደግሞም ፣ የቀድሞውን ፍርድና ቅጣት ፍርድ ቤቱ እግምት ውስጥ አላገባውም የሚል ግምት ቢኖረን እንኳን፣ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ ለሁለተኛው ወንጀል የሞት ቅጣት ሊፈጸምበት ይገባል የሚል አቋም ስለነበረው ምንም ዓይነት ልዩነት አይፈጥርም ነበር ። ስለዚህ ፣ ይግባኝ ባዩ በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1569/74 ጉዳይ በጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደተከራከረው ሁሉ ፣ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፈረዳቸው ሁለቱ ቅጣቶች በአንድነት ተፈጻሚ ስለማይሆኑ / ማለትም ተከሳሹ መጀመሪያ ለአሥራ አምስት ዓመት ታሥሮ ቀጥሎ ደግሞ በሞት አይቀጣም / የኋለኛው ቅጣት ፤ ማለትም የሞቱ ቅጣት ፍርድ ፣ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ጸንቶ ቢሆን ኖሮ ፣ የመጀመሪያውን ቅጣት ደርቦ ይይዝ ነበር።

ዳሩ ግን ፣ በሁለቱ ክሶች ላይ የጥፋተኝነት ፍርድ የተሰጠውና ቅጣት የተወሰነው በተለያየ[29] ጊዜ በመሆኑ ፣ ይግባኝ ባዩ በሁለቱም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ፍርዶች ላይ የተለያየ ይግባኝ ለማቅረብ ተገድዷል ። የወንጀል መዝገብ ቁጥር341/72 በከፍተኛው ፍርድ ቤት ገና በመታየት ላይ እንዳለ ፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ስድስተኛ ችሎት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 27/72 በተሰጠው ፍርድ ላይ የቀረበውን የወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1067/73 ን ይመረምር ነበር ። መዝገቡን በሚገባ ከመረመረ በኋላ ፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 522 መሠረት የጥፋተኝነቱን ፍርድ አጸናው ። ነገር ግን ፣ ቅጣቱን ከአሥራ አምስት ዓመት ወደ አሥር ዓመት ጽኑ እሥራት ይበልጥ አቃለለው።[30] ይህ ችሎት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1067/73[31] ላይ ፍርድ ሲሰጥ ሌላም ወንጀል አብሮ የተፈጸመ ለመሆኑ የሚያውቀው ነገር አልነበረም ።

ስድስተኛው ችሎት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1067/73 ላይ ፍርድ ከሰጠ በኋላ ፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፓነል ችሎት የወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1569/74ን[32] መርመረና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 113/2/ እና 195 /2/ /ለ/ /2/ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ፣ የጥፋተኝነት ፍርዱን ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር522 ወደ ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 8/67 አንቀጽ 3(2)[33] ለውጦ ይግባኝ ባዩን በአሥር ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ፈረደበት ።

እንግዲህ ፣ እላይ ከተገለጹት ፍሬ ነገሮች አንጻር ሲታይ ፣ በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1569/74 ጉዳይ ፣ ጭብጡ ከፍርድ በፊት የተፈጸመና ዘግይቶ የተገለጸ የተደራራቢ ወንጀል ጉዳይ እንደሆነ የፓነል ችሎት ያውቃል ፤ ወይም ማወቅ ነበረበት ፤ በማለት አንድ ሰው ሊገምት ይችላል ። ዳሩ ግን ፣ ምንም እንኳን ይግባኝ ባዩ በአንድ ቀን በሁለት ሰዓት ልዩነት ውስጥ ለተፈጸመ ለሌላ ወንጀል የጥፋተኝነት ፍርድ የተሰጠበት እና የተቀጣ መሆኑን የሚገልጽ አረፍተ ነገር በመዝገቡ ውስጥ በግልጽ ተጽፎ የሚገኝ ቢሆን ፣ ፍርድ ቤቱ ይህ ሁኔታ « በወግ » አልተነገረኝም ብሏል ። ይህ አባባል ፣ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በዚያ አረፍተ ነገር[34] ምን ለመጠቆም እንደተፈለገ መመርመር ከነበረበት ግዴታ አንፃር ሲታይ ፣ ተቀባይነት አይኖረውም ።

ይህ ሁኔታ ፣ ለፓነል ችሎት « በወግ » ተነግሮታል ፤ በስድስተኛው ችሎት ስለተሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ፍርድም ያውቃል ፤ ብንል እንኳን ፣ በወን ጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1569/74 ችሎቱ ቅጣቱን እንዴት መወሰን ይገባው ነበር ?

በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1067/73 ፣ ይግባኝ ባዩ በግፍ አገዳደል ወንጀል ፣ በቁጥር 522 መሠረት ፣ የጥፋተኝነት ፍርድ ተሰጥቶበታል ። ለዚህ ጥፋት በሕግ የተደነገገው ቅጣት ፣ የእድሜ ልክ እሥራት ወይም ሞት ነው ። እነዚህ ቅጣቶች ከዚህ በላይ ሊከብዱ አይችሉም ።[35] በዚህ ፋንታ ፣ ከተፈጸሙት ተደ ራራቢ ወንጀሎች ለአንደኛው ሕጉ ከእንዲህ ዓይነቶቹ ቅጣቶች አንዱን ደን ግን ሲገኝ ፣ እንዲህ ዓይነቱ ቅጣት ለሌሎቹ ተደራራቢ ጥፋቶች የተወሰኑትን ( ወይም የሚወሰኑትን ) ነጻነት የሚያሳጡ ቅጣቶች ሁሉ ደርቦ ይይዛል ።

ምንም እንኳን ፣ በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1067/73 ይግባኝ ባዩ በቁጥር 522 መሠረት የጥፋተኝነት ፍርድ ቢሰጥበት ፣ ከእድሜ ልክ እሥራት ወይም በሞት ከመቀጣት ይልቅ ፣ የቀለለ የአሥር ዓመት ጽኑ እሥራት ተወስኖ በታል ። ይህ የቅጣት ማቅለል የተደረገው ፣ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 79 እና 184 / ለ / ድንጋጌዎች መሠረት ነው ። በሌላ አነጋገር ፣ ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ባዩን በመጀመሪያ የእድሜ ልክ እሥራት ከፈረደበት በኋላ ፣ ቀጥሎ በቁጥር 79 የተገለጹትን የማቅለያ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ፣ ቅጣቱን አቅልሎለታል ። ይህ ከሆነ በኋላ ፣ የፓነል ችሎት የወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1569/74ን አይቶ፣ መዝገቡን ከመረመረ በኋላ ፣ የጥፋተኝነት ፍርድ የተሰጠበትን የሕግ ድንጋጌ ከወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 522 ወደ ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 8/67 አንቀጽ 3/2/ ለውጦ ፣ ይግባኝ ባዩ በአሥር ዓመት ጽኑ እሥ ራት እንዲቀጣ ወሰነ ። ሁኔታው ይህ ከሆነ ፣ የፓነል ችሎት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1067/73 ስለተሰጠው ፍርድ አውቆ ቢሆን ኖሮ ፣ ምን ማድ ረግ ይገባው ኖሯል ? ለወንጀሉ ከፍተኛውን ቅጣት ፣ ማለትም የአሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እሥራት ፣ ወስኖ ቅጣቱ ጐን ለጐን እንዲፈጸም ማዘዝ ይችል ነበር ? ወይስ ፣ በቁጥር 191 እና 189 መሠረት ቅጣቱን ያከብድ ነበር ? የዚህ ትችት አቅ ራቢ ፍርድ ቤቱ የትኛውንም ለማድረግ አይችልም ነበር የሚል አቋም አለው ። ሕጉ ሥልጣን ያልሰጠው በመሆኑ ፣ የመጀመሪያውን ለማድረግ አይችልም ነበር ። ከተፈጸሙት ተደራራቢ ወንጀሎች ለአንደኛው የተወሰነው ቅጣት በቁጥር 189 /1/ /ሀ/ የተገለጸው ዓይነት በመሆኑና ፣ ይህም ማናቸውንም ነፃነትን የሚያሳጡ ሌሎች ቅጣቶችን ሁሉ ደርቦ ስለሚይዝ ፣ የኋለኛውንም ማድረግ አይችልም ነበር ። በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ስለቅጣት ማክበድ አንናገርም ። በመሆኑም ፣ በተደራራቢ ወንጀሎች ጉዳይ ፣ ከተፈጸሙት ተደራራቢ ወንጀሎች ለአንደኛው የእድሜ ልክ እሥራት ወይም የሞት ቅጣት ተደንግጎ ከሆነ ፣ ሌሎቹ ተደራራቢ ወንጀሎች ሊኖ ራቸው የሚችለው አግባብነት ፣ ቅጣቱ የሚቀልበትን መጠን ለመወሰን ብቻ ነው ። ስለዚህ፣ ምንም እንኳን በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1067/73 ለተገለጸው ወንጀል ቅጣት ለመቁረጥ በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1569/74 የተገለጸው ወንጀል አግባብነት ያልነበረው ቢሆን ፣ ቅጣቱ የሚቀልበትን መጠን ለመወ ሰን ግን አግባብነት ይኖረው ነበር ። ስድስተኛው ችሎት የሁለተኛውን ወን ጀል መፈጸም አውቆ ቢሆን ኖሮ ፣ ቅጣቱን በማቅለል እረገድ ፣ ምናልባት እስከ ዝቅተኛው መጠን አይወርድም ነበር ። ዳሩ ግን ፣ የእንዲህ ዓይነቱ የቅጣት ማክ በድ ምክንያት መኖር እንኳ ፣ የቅጣት ማቃለያ ምክንያቶችን ገምግሞ ፣ በቁጥር 184 ሥር እተደነገገው እጅግ ዝቅተኛው የቅጣት መጠን ድረስ ቅጣቱን ከማቅ ለል ፣ ፍርድ ቤቱን የማያግደው መሆኑንም ማወቅ ይኖርብናል ።

ስለዚህ ፤ በዚህ ልዩ ጉዳይ ፤ ፍርድ ቤቱ ለጉዳዩ አግባብነት በሌለው በቁጥር 189 / 1 / / ለ / መሠረት የቅጣቱን መጠን ከማሳደግ ፋንታ ፤ በቁጥር 522 ለግፍ አገዳደል የተቆረጠው ቅጣት ፤ በልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 8/67 በአንቀጽ 3/2/ ፤ ጦር መሳሪያ ይዞ ለሚደረግ የአመጽ ተግባር የተቆረጠውን ቅጣት ደርቦ ይይዛል ፤ የሚል ፍርድ መስጠት ነበረበት ።

## መ ደ ም ደ ሚ ያ

ነጻነትን የሚያሳጡ ቅጣቶችን የሚያስከትሉ ተደራራቢ ወንጀሎች በሚያጋጥሙበት ጉዳይ ፤ ቅጣቱ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በቁጥር 189 / 1 / / ሀ—ለ / መሠረት መወሰን ይገባዋል ። ተከሳሹ ከተከሰሰባቸው ተደራራቢ ወንጀሎች መካከል ፤ ለአንደኛው ሕጉ የደነገገው ቅጣት የእድሜ ልክ እሥራት ወይም ሞት ሆኖ ሲገኝ ፤ እነዚህ ቅጣቶች ፤ ሌሎች ነጻነትን የሚያሳጡ ቅጣቶችን ሁሉ ደርበው መያዝ ይኖርባቸዋል ። በሌሎች ሁኔታዎች ፤ ቅጣቱ የቁጥር 189 ንዑስ ቁጥር / 1 / / ለ / ድንጋጌዎችን በመከተል መወሰን ይኖርበታል ።

በዚህ ልዩ ጉዳይ ፤ ፍርድ ቤቱ « መሠረታዊው ቅጣት » ከሁሉ ይልቅ ከባድ ለሆነው ወንጀል በሕግ የተወሰነው ከፍተኛው ቅጣት ነው ፤ ብሎ በመፍረድ ፋንታ ፤ ከሁሉ ይልቅ ከባድ ለሆነው ወንጀል ፍርድ ቤቱ የሚወስነው ቅጣት ነው ፤ የሚለውን አቋም በመወሰዱ ተሳስቷል ። ፍርድ ቤቱ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚ ለያደርገው ከሚገባው የአማርኛው ቅጂ አንጻር ሲታይ ፤ ይህ አቋም ተቀባይነት የሚኖረው አያሆንም ። እንዲሁም ፤ ለዚህ ጉዳይ ቅጣቱን ለመወሰን አግባብነት ያለው ቁጥር 189 /1/ /ለ/ ነው ፤ የሚለውን አቋም በመውሰዱም ፤ ፍርድ ቤቱተሳስቷል።

ይሁን እንጂ ፤ ሁለቱ ክሶች በአንድ ላይ ታይተው ቢሆን ኖሮ ፤ ከተደራራቢ ወንጀሎቹ አንደኛው የሚያስከትለው ዝቅተኛ ቅጣት የእድሜ ልክ እሥራት በመሆኑ ፤ ቅጣቱ በቁጥር 189 / 1 / / ሀ / መሠረት መወሰን ይገባው እንደነበረ አሁን ግልጽ መሆን አለበት ። ይግሞም ፤ ሁለቱ ክሶች በተናጠል ታይተው ቢሆንም እንኳን ፤ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 191 በሚያዘው መሠረት ፤ ቅጣቱን ለመቁረጥ ተፈፃሚ ይሆን የነበረው ይኸው ድንጋጌ ነበር ። ይሁን እንጂ ፤ በኋለኛው ሁኔታ ፤ ፍርድ ቤቱ በይግባኝ ባዩ ላይ ፤ የልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀጽ 3/2/ን ድንጋጌ ተላልፏል ፤ የሚል የጥፋተኝነት ውሳኔ ከመስጠት በቀር ፤ አንዳች ሌላ ነገር ማድረግ አይችልም ነበር ።

ቁጥር 191 በሁለቱ ፍርዶች የተነሳውን ሁኔታ ሙሉ በሙሉ እንደማይሸፍን ግልጽ ነው ። ምንም እንኳን በዚህ ጉዳይ የተነሳው ችግር በቁጥር 522 ሥር ለግፍ አገዳደል የተቆረጠው ቅጣት ፤ ጦር መሳሪያ በመያዝ ለተደረገው የአመጽ ተግባር የተቆረጠውን ቅጣት ደርቦ ይይዛል ፤ የሚል ፍርድ በመስጠት ይፈታ የነበረ ቢሆን ፤ ፍርድ ቤቱ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 191 ሥር በተገለጸው ተመሳሳይ ሁኔታ ወደ ስሕተት ተመርቷል ።

ስለዚህ ፤ እንዲህ ያለውን አሻሚ ሁኔታ ለማስወገድ ፤ በዚህ ጉዳይ የተነሳውን ሁኔታ የሚሸፍን ደንጋጌ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ውስጥ ማስገባቱ ተገቢ ይሆናል ።

የዚህ ትችት አቅራቢ ፤ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉንና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ—ሥርዓቱን እንዲያሻሽል ሥልጣን የተሰጠው ኮሚቴ ፤ ሁኔታውን በመገምገም ፤ ቀዳዳውን የሚሸፍን አንድ ዓይነት ደንጋጌ ፤ ለምሳሌ በስዊድን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፤ በምዕራፍ 34 ፤ ክፍል 10 ፤ በአንቀጽ ሁለት ፤ የተደነገገውን የሚመስል ደንብ ፤ ያስገባል ብሎ ተስፋ ያደርጋል ።

# የግርጌ ማስታወሻዎች

* የሕግ ሌክቸረር ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ።

1. ግዙፋዊ በሆነ መደራረብ ጊዜ ፣ ተከታታይ (ማለትም በርካታ) ድርጊቶች እንዲኖሩ ያስፈልጋል ። ድርጊቱ አንድና ፣ አንድን የወንጀል ድንጋጌ ብቻ የሚጥስ ከሆነ ፣ ድርጊቱ በተለያዩ ሰዎች ላይ ቢፈጸምም እንኳን (ለምሳሌ «ወ» ከሚግጡበት መስክ የ«ሀ»ን በሬ የ«ለ»ን ላምና የ«መ»ን ፈረስ ቢሰርቅ) ጥፋተኛው የሚከሰሰው ለአንድ ወንጀል ብቻ ነው ።

2. «ወ» በ«ተ» ላይ የፈጸማቸው የተለያዩ ስርቆቶች በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 61 በተገለጸው መሠረት ፣ለአዲስ የወንጀል፡ መፈጸም ሀሳብ የተፈጸሙ መሆን አለባቸው ። ይሩ ግን የ«ወ» ከ«ተ» ላይ በመደጋገም እቃዎችን የመስረቅ ድርጊቶች የተፈጸሙት «« በዚያው በመጀመሪያው የወንጀል ሀሳብና .... አንድን ግብ ለማግኘት .... ከሆነ »» ማለትም የማይገባውን ብልጽግና ለማግኘት (ለምሳሌ «ወ» ያሰበው እንበል አምስት ጆንያ ስንዴ ከ«ተ» ጉተራ ለመስረቅ ሆኖ በአምስት የተለያዩ ወቅቶች ስንዴውን ከ«ተ» ጉተራ ቢወስድ) ድርጊቶቹ እንደ አንድ ጥፋት ሆነው ይታያሉ እንጂ እንደ ተደራራቢ ጥፋት አይቆጠሩም ። የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 60(2)ን ይመለከቷል ።

3. ግን በሁለቱም ሁኔታዎች ተከታታዮቹ የወንጀል ድርጊቶች ጥፋተኛው ለአንደኛውም ተግባሩ ተከስሶ የጥፋተኝነት ውሳኔ ሳይሰጥበት በፊት የተፈጸሙ መሆን እንዳለባቸው መገንዘብ ያሻል ። ሁለተኛው ወንጀል ከመፈጸሙ በፊት ጥፋተኛው በመጀመሪያው ወንጀል የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶበት ከተቀጣ ፣ ጉዳዩ የወንጀል መደራረብ በመሆን ፈንታ ፣ የጥፋት መደጋገም ይሆናል ። የጥፋት መደጋገም የሚኖረው የጥፋተኝነት ፍርድና ቅጣት የሁለት ወንጀሎችን መፈጸም የሚለያዩዋቸው ሲሆን ነው ።

4. የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርት ቁጥር 116 (1) ።

5. የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርአት ቁጥር 115 (2) ። ወንጀሎቹ በተለያዩ ጊዜያት የተፈጸሙና ግንኙነት የሌላቸው ከሆነ ተከሳሹ መከላከያውን በማቅረብ ረገድ ችግር እንዳይገጥመው የተለያየ ክስ እንዲቀርብ ማዘዝ አግባብ መስሎ ይታያል ። በዚህ አጋጣሚም ፣ በአማርኛውና በእንግሊዝኛው የዚህ ንዑስ አንቀጽ ቅጅ መካከል ያለውን ልዩነት መገንዘብ ተገቢ ይሆናል ። በአማርኛው ቅጅ መሠረት ተደራራቢ ወንጀሎችን በአንድነት ማ... ... በእንግሊዝኛው ቅጅ ግን የምርጫ ጉዳይ ነው ።

6. በአንድ ክስ መታየቱ ቀርቶ የተካሳሹ ጉዳይ በተከታታይ ክሶች የሚታይ ቢሆን እንኳን በተከሳሹ ላይ ቅጣቱ እንዴት ይወሰናል ? የመጨረሻው ክስ ፍጻሜ እስኪያገኝ ድረስ ለሌሎቹ ወንጀሎች ቅጣት የመቁረጡ ጉዳይ ሊዘገይ ይገባዋልን ? የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ሥነ ሥርአቱ እነዚህን ጥያቄዎች አይመልስም ። ስለዚህ በህግ (ማለትም በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 189) ከተገለጸው የቅጣት አወሳሰን ዘዴ አንጻር ሲታይ የመጨረሻው ክስ ፍጻሜ እስኪያገኝ ድረስ ለሌሎቹ ወንጀሎች ቅጣት የመቁረጡን ተግባር ማዘግየቱ ትክክለኛ አሠራር ይመስላል ። ቅጣት የመወሰን ሥልጣን ሊኖረው የሚገባውም ፍ/ቤት ከሁሉ ይልቅ ከባድ የሆነውን ወንጀል የሚያየው መሆን ይኖርበታል።

7. ለምሳሌ በኮመን ሎ አንድ ተከሳሽ በተደራራቢ ወንጀሎች በፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሲሰጥበት ዳኛው ለእያንዳንዱ ወንጀል የተቆረጠውን ቅጣት በማዳመር በጥፋተኛው ላይ የተዳመረ ቅጣት ሊወስንበት ይችላል ። ይሁን እንጂ ዳኛው ቅጣቶቹ በተከታታይ እንዲፈጸሙ በግልጽ ካላዘዘ በቀር ድርብርብ ቅጣቶች መፈጸም ያለባቸው ጐን ለጐን ነው ። እንዲሆም የወንጀል ድርጊቶቹ ከአንድ ሁኔታ ከመነጩ (ማለትም በአንድ ጊዜ ወይም የአንድ ክንዋኔ ክፍል ሆነው ከተፈጸሙ) የቅጣት ዘመኖቹ በተከታታይነት ሳይሆን ጐን ለጐን የሚቆጠሩ ይሆናል ። ሶል ሩቢን <u>ዘሎ ኦቭ ክሪሚናል ኮሬክሽን</u> (ሴንት ፓል ሚን ዌስት ፓብሊሺንግ ካምፓኒ 1963) ገጽ 415 ፣ እና ሰር ሩፐርት ክሮስ ፣ <u>ዘ ኢንግሊሽ ሴንተንሲንግ ሲስተም</u> ፣ (ለንደን በተርወርዝስ ፣ 1981) ገጽ 100 ይመለከቷል ።

8. ለምሳሌ የሶቪዬት ኀብረት የፌዴራል የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 35ን ይመለከትዋል ።

9. ይህ አባባል በኮመን ሎ በሠፊው የሚሠራበትን ተከሳሹን በገደብ ነጻ የመልቀቅ ልምድ ሳይመለከት ነው ።

10. ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 8 የተጠቀሰውን ገጽ 102 ይመለከቷል ።

11. የ1923ቱ የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር ፬፻ የሚከተለውን ይደነግጋል ።

> « አንድ ሰው ብዙ ዓይነት ወንጀሎች ሠርቶ በሠራቸው ወንጀሎች ሁሉ በአንድ ጊዜ የተከሰሰባቸው እንደሆነ ፣ በእያንዳንዱ ወንጀል እንደደንቡ ይነጋገራል ። ስለሆነ ግን ከነዚሁ ከተከሰሰባቸው ወንጀሎች ለትልቁ ወንጀል በተወሰነው ደንብ ይቀጣል እንጂ በሁሉም ለየብቻው አይቀጣም ። ... የትንንሽ ደንብ ተላላፊዎች ቅጣት ግን በየወንጀሉ ተደምሮ ይቀጣል ። ስለሆነ የቅጣቱ ዘመን ከሁለት ዓመት አያልፍም ።»

12. የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 725ን ይመለከቷል ። እንዲህ ያሉ ጥፋቶችን በሚመለከት ፣ የማዳመር ዘዴ በሥራ ላይ እንዳለ እንዲቆይ የተደረገበት ምክንያት በህግ የተደነገገው ከፍተኛ የቅጣት ዘመን የሶስት ወር እሥራት በመሆኑ ( የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 703/1/ን ይመለከቷል ) ቢዳመር እንኳን ረዥም ስለማይሆን ይመስላል ።

13. በተጨማሪ የወንጀል መደራረብ ጊዜ ቅጣት የማክበዱ ጉዳይ ለፍርድ ቤቱ መልካም ፈቃድ የተተወና የሚታዘዘውም « የተፈጸመው ጥፋት ወንጀለኛው ለህጉ ያለውን ንቀት ሲያንጸባርቅና ቅጣቱን ለማክበድም አጥጋቢ ምክንያት ሆኖ ሲገኝ » ብቻ ነው ። ሆኖም ህጉ በግልጽ በሚደነግግበት ጊዜ ( ቁጥር 63/2/) ቅጣቱ የግድ መክበድ ያለበት መሆኑን መገንዘብ ያሻል ። የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 692ን ይመለከቷል ።

14. በትክክለኛ አስተሳሰብ ከሆነ ፣ ይህ የእድሜ ልክ እሥራትንም መጨመር ይኖርበታል ።

15. አንዳንድ ሰዎች ይህን ማጠቃለል ነው ብለው ያስቡ ይሆናል ፤ ዳሩ ግን ፣ አንድ ሰው ከህይወት ዘመኑ በላይ ሊታሰር ስለማይችል ፤ ከአንድ ጊዜ በላይም በሞት ሊቀጣ ስለማይችል ፣ በእድሜ ልክ እሥራትና በሞት ቅጣት ሁኔታ ፣ ስለማዳመርም ሆነ ስለማጠቃለል ፣ ሌላው ቀርቶ ስለማክበድም ቢሆን እንኳን ፣ መናገር እንደማንችል መገንዘብ ይገባል ።

16. የአማርኛው ቅጅ « በአጋማሹ » ከማለት ፋንታ ፣ « እስከ አጋማሹ » ይላል ። የሁለቱ ቅጆች አነጋገር የሚያስከትለው ውጤት ፣ የእንግሊዝኛው ቅጅ ተፈጻሚነት የሚኖረው ከሆነ ፣ የቅጣቱን ዘመን ማራዘም አግባብ በሚሆንበት ጊዜ ፣ መሠረታዊውን ቅጣት ሁልጊዜም የግድ በግማሽ መብለጥ ይኖራል። የአማርኛው ቅጅ ተፈጻሚነት የሚኖረው ከሆነ ግን፣ መሠረታዊውን ቅጣት ሁልጊዜ የግድ በአጋማሹ ማሳደግ አያስፈልግልም ። ሕጉ ፍ/ቤቱ «እስከ አጋማሹ» ድረስ ማሳደግ ይችላል ስለሚል ፣ አንዳንድ ጊዜ ከአጋማሹ በአነሰ ዘመንም ለማሳደግ ይቻላል ።

17. የስዊስ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 66/1/ን እና ፊሊፕ ግራቨን ፣ አን ኢንትሮዳክሽን ቱ ኢትዮፒያን ፒናል ሎ ፣ ( አዲስ አበባ ፣ ህግ ፋክልቲ ፣ ቀ.ኃ.ሥ. ዩኒቨርሲቲ ፣ 1965 ) ገጽ 258ን ይመለከቷል ።

18. አነስተኛው ድምጽ በዚህ ነጥብ ላይ አንዳች የተናገረው ነገር የለም ። በሌላ በኩል ፣ አቃቤ ህጉ መሠረታዊው ቅጣት ከሁሉ ይልቅ ከባድ ለሆነው ወንጀል በህግ የተደነገገው ቅጣት ነው እንጂ ፣ በፍ/ቤቱ የተወሰነው ቅጣት አይደለም ፤ በማለት ያቀረበው ክርክር ትክክል ነው ። ይሁን እንጂ ፣ ፍ/ቤቱ ቅጣቶቹን እንዲያዳምርለት በመጠየቁ ተሳስቷል ።

19. ለዚህ ጥፋት በህግ የተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት የአሥራ አምስት ዓመት እሥራት ሲሆን ፣ ለቃጠሎ ወንጀል ግን የአሥር ዓመት እሥራት ነው ።

20. በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 107 መሠረት ፣ የጽኑ እሥራት ዘመን እርዝመት ከአንድ እስከ ሃያ አምስት ዓመት ነው ።

21. የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 191/ 1 / ን ይመለከቷል ።

22. የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 191 / 2 / ።

23. ለምሳሌ የሪፐብሊክ ቻይናን የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 53ን እና የሲዊድንን የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ምዕራፍ 34 ፣ ክፍል 10 ፣ አንቀጽ ሁለትን ይመለከቷል ።

24. ዳሩ ግን ፣ ተከሳሹ ከተደራራቢ የወንጀል ድርጊቶቹ መካከል በጥቂቶቹ ተከሶ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 189 / 1 / / ለ / መሠረት ቅጣት የተቀረጠበት ከሆነ ፣ ዘግይቶ የተገለጸው የወንጀል ድርጊት ከሁሉ ይልቅ ከባድ ካልሆነ በቀር፣ ፍ/ቤቱ ሌላ የወንጀል ድርጊት መፈጸሙን ዘግይቶ የደረሰበት በመሆኑ ብቻ ፣ አዲስ ቅጣት ለመወሰን እንደማይችል መገንዘብ ይገባል ።

25. ይህ መዝገብየተከፈተው በጥቅምት 13 ቀን 1972 ዓ.ም. ነበር ።

26. ይህ መዝገብ የተከፈተው በሰኔ 11 ቀን 1972 ዓ.ም. ሲሆን ፣ ወንጀሉ የታወቀው በወንጀል መዝገብ ቁጥር 27/72 የቀረበው ክስ መታየት ከጀመረ በኋላ ነው ፤ የሚለውን ግምት ያጠናክራል ።

27. አቃቤ ህጉ በተከሳሹ ላይ እነዚህን ቁጥሮች ሲጠቅስ ፣ መሳሳቱን ይገነዘቧል ። የጉዳዩ ፍሬ ነገሮች ሲመረመሩ ፣ እነዚህን ቁጥሮች ከመጥቀስ ፋንታ፣ቢያንስ ቢያንስ ፣ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 637 / 2 / ን መጥቀስ በተገባው ነበር ።

28. ሁለቱ ክሶች በታዩና በተወሰኑ ጊዜ ፣ ሰብሳቢው ዳኛ አንድ እንደነበሩ በዚህ አጋጣሚ ይገነዘቧል ።

29. የወንጀል መዝገብ ቁጥር 27/72 የተወሰነው ኅዳር 10 ቀን 1973 ዓ.ም. ሲሆን ፣ የወንጀል መዝገብ ቁጥር 341/72 ደግሞ የተወሰነው ከአንድ ዓመት ገደማ በኋላ በመስከረም 27 ቀን 1974 ዓ.ም. ነው።

30. የከፍተኛው ፍ/ቤት በመጀመሪያ ቅጣቱን ከእድሜ ልክ እሥራት ወደ አሥራ አምስት ዓመት ፀማቅለል ዝቅ አድርጐ ወስኖት የነበረ በመሆኑ ነው ይህ ይበልጥ ማቅለል የሚሆነው ።

31. ይህ ይግባኝ የተወሰነው ሰኔ 23 ቀን 1974 ዓ.ም. ነው ።

32. ይህ ይግባኝ የቀረበው ከፍተኛው ፍ/ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 341/72 በሰጠው ፍርድ ላይ ነው ።

33. ይህ ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ ፣ በፈቃደኛነት የጦር መሳሪያ በመያዝ የመንግሥት ላይ ለሚደረግ የአመጽ ሥራ ፣ ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ያስቀጣል ።

34. በከፍተኛው ፍ/ቤት መዝገብ ላይ የሠፈረው ቃል የሚከተለው ነው ።

> « ሁለተኛው ተከሳሽ ድሪባ አቦልቱ ይኸንን ወንጀል በፈጸመበት እለት ፣ ማለት በሰዓት ልዩነት ፣ ጥር 13 ቀን 1969 ዓ.ም. ከቀኑ 12 ሰዓት በሚሆን በት ጊዜ ፣ ከሌላ የወንጀል ግብረ አበሩ ጋራ በውንብድና ተግባር ተሰማርቶ ፣ እሸቴ ወልደየስ ይባል የነበረውን በመግደሉ ፣ በዚሁ ፍ/ቤት በወንጀል መዝ ገብ ቁጥር 27/72 በሆነ ክስ ቀርቦበት ፣ የ15 ዓመት እሥራት የተወሰነበት ሪከርድ ያለው የተደጋገመ ጥፋተኛ ለመሆኑ ፍ/ቤቱ መዝገቡን ተመልክቶ ፣ . . . . የህጉ ክፍል በሚያዘው ከፍተኛ ቅጣት ፣ የጥፋተኝነት ውሳኔ በተሰ ጠበት አንቀጽ እንዲወሰንበት አቃቤ ህግ ያሳስባል ። »

35. የእድሜ ልክ እሥራትን በማከበድ ወደ ሞት ቅጣት ለመለወጥ ይቻላል ይባል ይሆናል ። ይሁን እንጂ ፣ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 189 መሠረት ይህ እንደማይቻል መገንዘብ ይኖርብናል ። በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ /ሀ/ መሠረት ፣ ፍ/ቤቱ የሞት ቅጣት ሊፈርድ የሚችለው ፣ ህጉ ከተደራራቢ ወንጀሎቹ መካከል ለአንዱ ይህንን ቅጣት ሲወስን ብቻ ነው ። ምንም እንኳን ህጉ ለከፍተኛው ተደራራቢ ወንጀል እንደ እድሜ ልክ እሥራት ወይም የሞት ቅጣት የመሳሰሉትን አማራጭ ቅጣቶች ቢወስን ፣ ተከሳሹ ተደራራቢ ጥፋት ፈጽሟል በሚል ምክንያት ብቻ ፣ የሞት ቅጣት አይፈረድበትም ። በዚህ ዓይነቱ ጉዳይ ፣ በሞት ቅጣት ፋንታ የእድሜ ልክ እሥራት መፍ ረድ ይቻላል ። ደግሞም ፣ ይህ ፍርድ እንደዬ ከተፈረደ ፣ ተከሳሹ በጥፋቱ ቅጣት ከተፈረደበት በኋላ በሞት የሚያስቀጣ ሌላ ጥፋት ካልፈጸመ ፣ ወይም የጥፋተኛነት ውሳኔ ከመሰጠቱ ቀደም ብሎ በሞት የሚያስቀጣ ሌላም ወንጀል ፈጽሞ እንደነበረ ዘግይቶ ካልተገለጸ በቀር ፣ ወደሞት ቅጣት ሊለወጥ አይችልም ።

በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1067/73 ይግባኝ ባዩ በእድሜ ልክ እሥራት ወይም በሞት ቅጣት በሚያስቀጣው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 522 መሠረት የተፈረደበት መሆኑን ማስታወስ ይኖርብናል ። ነገር ግን ፣ በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1569/74 ፣ ከአሥራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት በሚያስቀጣው በልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ አንቀጽ 3/2/ ሥር ፣ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶበታል ። ይህም ማለት ፣ ሰድስተኛው ችሎትም ሆነ የጠቅላይ ፍ/ቤት ፓነል ችሎት ፣ ዘግይቶ በልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 8/67 በአንቀጽ 3/2 መሠረት ይግባኝ ባዩን ጥፋተኛ ሲያደርግ ፣ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 522 መሠረት የተቆረጠውን ቅጣት ለመለወጥ ሥልጣን አልነበረውም ።